


በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህል፣
ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ
በሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን ምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ የጎደቤ
ታላቢ ብሔራዊ ፓርክ ዝርዝር ጥናት ሪፖርት
የዱር እንስሳት ጥናት፣ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዋና የስራ ሂደት
የካቲት/2007
ባህርዳር


የጥናት ጽሑፍ አዘጋጆች፡-
❖አቶ አበጀ ዘውዴ
❖አቶ ቀናው አበጀ
❖አቶ ብርሃነመስቀል ዓለሙ

ማውጫ

ገጽ

1. መግቢያ 1

1.2. የጥናቱ አስፈላጊነት 2

1.3. ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ አጠቃላይ ሁኔታ 3

1.3.1 መገኛና ስፋት 3

1.3.2 የአየር ንብረት 4

1.3.3 የመሬት አቀማመጥና የአፈር አይነት 4

1.4. የጥናቱ ዓላማ 5

1.4.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ 5

1.5. የጥናቱ ስልቶችና ቁሳቁሶች 5

1.5.1 ጥቅም ላይ የዋሉ ዋና ዋና ማስፈፀሚያ ስልቶች 5

1.5.2 ለጥናቱ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች 6

1.5.3 የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት 6

2. የጥናቱ ውጤት 7

2.1 ስለ ተፈጥሮ ደኑ የጥበቃ ስልትና ታሪክ 7

2.2 የስርዓተ ምህዳር ሁኔታ 8

2.3 የዱር እንስሳት 9

2.4 የዕፅዋት ሽፋንና ዓይነት 11

2.5. በታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩ ዙሪያ የሚኖሩ ህዝቦች አኗኗር ሁኔታና የሚያደርሱት ተጽዕኖ 12

2.5.1.የአካባቢው ነዋሪዎች ሁኔታ 12

2.5.2.በታሣቢ ጥብቅ ሥፍራው የተፈጥሮ ሃብት ላይ የሚታዩ ጫናዎች/ተጽዕኖዎች 17

2.6.የቱሪዝም አቅም ጥናት 21

3. የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ የሚኖረው ጠቀሜታ 37

4. ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች 39

5. የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ጠቀሜታና ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች ጥምረት ዝምድና 42

6. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች 46

7. ወደፊት መከናወን ያለባቸው ስራዎች 47

8. የጉዳዩ ባለቤቶችና የባለድርሻ አካላት ተግባራትና ኃላፊነት ትንተና 49

8.ዋቢ መጽሐፍት (References) 55

እዝል1. በጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በጥናት ወቅት የተለዩ ዕፅዋት 58

እዝል2. በጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በጥናት ወቅት የተለዩ የዱር እንስሳት.....61
እዝል3. በጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በጥናት ወቅት የተለዩ አዕዋፍት.....63
ዕዝል 5 በጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክና አካባቢው ጠቃሚ የሆኑ ዋና ዋና የጂፒኤስ ነጥቦች/ንባቦች...65

1. መግቢያ

የብዝሃ ህይዎት ሃብቶች ለህይዎት ሂደቶች እጅግ አስፈላጊ ከመሆናቸዎ በላይ ለሰው ልጅ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ማህበራዊ ልማትና እድገት እጅግ ወሳኝ ናቸው። ሆኖም ግን በአሁኑ ወቅት ብዝሀ ህይወት ከመደበኛው የዝርያዎች የመለወጥና የመጥፋት ሂደት ከ1000 እጥፍ በላይ የፈጠነ እንደሆነ ምሁራን ይናገራሉ። ከእነዚህ የጥፋት ምክንያቶች ውስጥ ዋነኛው የሰው ልጆች ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት በመጨመሩ የተነሳ መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የዱር እንስሳት መራቢያ፣ መጠለያና መመገቢያ የሆኑት የተፈጥሮ አካባቢዎች በማውደማቸው እንደሆነ ይነገራል። በመሆኑም ጥብቅ ሥፍራዎች ምቹንና ብዝሀ ህይዎትን በመጠበቅ ዘላቂነት ያለው አጠቃቀም እንዲጎለብት ጠቀሜታቸው የጎላ ነው። በዚህ ክፍለ ዘመን ጥብቅ ስፍራዎችና የብዝሀ ህይወት ሃብቶች ለምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች መሳካት ዋና መሰረቶች መሆናቸውንና እነሱን በአግባቡ መጠበቅና መጠቀም ካልቻልን ልናሳካቸው እንደማንችል የዓለም ማህበረሰብ የተረዳበትና ዘላቂነት ያለው የሀብት አጠቃቀም ማስፈን ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን የተገነዘቡበት ወቅት ነው።

በክልሉ የሚገኙ በርካታ የተፈጥሮ አካባቢዎች ለረጅም ዓመታት በሰው ልጆች ተዕዕኖ ውስጥ ወድቀው ቆይተዋል። መሬቱና በውስጡ የሚገኙ ሌሎች የተፈጥሮ ሐብቶች በከፍተኛ ሁኔታ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። በአሁኑ ጊዜ በክልሉ 5 ብሄራዊ ፓርኮች እና አንድ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ያሉ ሲሆን ይህም በIUCN መስፈርት መሰረት ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ቢያንስ 10 ከመቶ መሸፈን ያለበት ቢሆንም እነዚህ ጥብቅ ስፍራዎች ከጠቅላላ የክልሉ ቆዳ ስፋት የሚሸፍኑት 2.5 ከመቶ ብቻ ነው። ሆኖም ግን ከአሁን በፊት የጥናት ስራቸው የተጠናቀቁት የወፍ ዋሻ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ፣የወለቃ አባይና በቶ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ፣የጉና ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ፣የአቡነ የሴፍ፣አቦይ ጋራና ዝጊት ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ፣የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራና አሁን የጥናት ሰነዱ የተዘጋጀለት የጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ህጋዊ እወቅና ማግኘት ቢችሉ የክልሉን የጥብቅ ስፍራ ሽፋን ወደ 3.134 ከመቶ ከፍ ያደርገዋል።

ቢሮው በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት አንዱ በክልሉ ውስጥ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ያላቸውን ቦታዎች በማጥናትና በመከለል ህጋዊ እውቅና እንዲያገኙ ማስቻል ነው። በዚህ መሰረት በሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን በምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን የጎደቤን የተፈጥሮ ደንና አካባቢውን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ለማረጋገጥ የሚያስችል

የመጀመሪያ ደረጃ ጥናት ተከናውኗል። የጎደቤ የተፈጥሮ ደንና አካባቢው በዋናነት የ Sudan–Guinea Savanna ባዮም እና *Combretum-Terminalia* Woodland ስርዓተ ምህዳርን የሚወክል ሲሆን የስርዓተ-ምህዳሩ መገለጫ የሆኑትን እንደ የአባሎ ዝርያዎች፣ ዛና፣ ሽመል፣ ክርክራ፣ ዋልያ መቀር የመሳሰሉትን የዕፅዋት ዝርያዎችን አቅፎ የያዘ ሲሆን ይህ ስርዓተ ምህዳር በጋምቤላ ብሄራዊ ፓርክ፣ በባጉሳ ብሄራዊ ፓርክ እንዲሁም በአላጥሽ ብሄራዊ ፓርክ በከፊል የተወከለ ሲሆን የጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ወደ ጥብቅ ስፍራነት ደረጃ ማደግ የበረሃማነት መስፋፋትን እንደመቀነት በመሆን ሲከላከል የቆየውንና አሁን በመቆረጥ ላይ ያለውን መቀነትና የአባሎ-ወይባን /*Combretum-Terminalia* Woodland/ ስርዓተ ምህዳር የጥበቃ ሽፋን ያሰፋዋል።

ይህ የተፈጥሮ አካባቢ ብሄራዊ ፓርክ ሆኖ መጠበቁ በዋናነት አካባቢው ለብዝሃ ህይዋት ልማትና ጥበቃና ለኢኮቱሪዝም ልማት ከመዋሉ ባሻገር የሚከተሉትን ዝርዝር ጠቀሜታዎች ሊሰጥ ይችላል እነሱም የዱር እንስሳት፣ የእጽዋትና ደቂቅ ዘአካላት ተለያይነት እንዲኖር ስለሚያስችል፤ ብርቅየና ለመጥፋት የተቃረቡ የብዝሃ ህይዎት ዝርያዎች የመጠበቂያና የመኖሪያ ስፍራ በመሆን ሊያገለግል ስለሚችል፤ ድንበር ተሻጋሪ የዱር እንስሳት በተለይም ወፎች የመራቢና የመመገቢያ ስፍራነት በመሆን ሊያገለግል ስለሚችል፤ ያልተጠበቁ ክስተቶች እንደድርቅ፣ በሽታ ወረርሽኝ፣ የሙቀት መጨመር በሚኖርበት ወቅት በውስጡ ያሉ የብዝሃ ህይዎት ሃብቶች ተፈጥሯዊ የመቋቋም አቅማቸው እንዲጨምር የሚስችል በመሆኑና ለሰው ልጅ ህልውና አስፈላጊ የሆኑ ዝርያዎችን እንደማቆያ ማዕከል ሆኖ ሊያገለግል ስለሚችል ይህ ጥናት ተከናውኗል።

1.2. የጥናቱ አስፈላጊነት

- በክልሉ ያሉ የጥብቅ ስፍራዎችን ቁጥር በመጨመር በክልሉ የሚገኘውን ወካይ የተፈጥሮ ስርዓተ ምህዳር የጥበቃ ሽፋን ማሳደግ በማስፈለጉ፣
- የአካባቢው ስርዓተ ምህዳር (Sudano-Guinean biome) በእርሻ መስፋፋት፣ ህገ ወጥ አደን፣ሰደድ አሳት፣ ሰፈራ እና ደን ጭፍጨፋ ምክንያት ከፍተኛ ችግር እየደረሰበት ያለ በመሆኑ የችግሩን መነሻና መፍትሄ ለማፈላለግ ጥናት ማድረግ በማስፈለጉ፣
- በውስጡ የሚገኘውን የብዝሃ ህይወት ሃብት አቅም ማወቅ በማስፈለጉ፣
- የተፈጥሮ ደኑን አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና የቱሪዝም ጠቀሜታና አቅም ማወቅ በማስፈለጉ፣


- ጥብቅ ስፍራውን ህጋዊ እውቅና ለማሰጠት በወረዳው የተከናወነው የክለላ ስራ በአግባቡ የተከናወነና በቂ መሆኑን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፣

1.3. ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ አጠቃላይ ሁኔታ

1.3.1 መገኛና ስፋት

የጎደቤ የተፈጥሮ ደን በሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን በዋናነት በምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የመተማ ወረዳም ያዋስነዋል። ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በሁለት ወረዳዎች ውስጥ ከሚገኙ ስድስት ቀበሌዎች ጋር የሚዋሰን ነው። ጠቅላላ ስፋቱም ከ18987 ሄ/ር በላይ እንደሚደርስ የወረዳው አጋር አካላት ያደረጉት የክለላ ጥናት ውጤት ያመለክታል። አካባቢው በሰሜን ምዕራብ የልማት ቀጠና ውስጥ ይገኛል።

የጎደቤ የተፈጥሮ ደን የሚገኘው ከጎንደር ወደ ሁመራ በሚወስደው የአስፓልት መንገድ 120 ኪ.ሜ. ላይ ሶረቃ ከተማ ሲደርሱ ወደምራብ በመታጠፍ ያለውን የጠጠር መንገድ 80 ኪ.ሜ እንደተጓዙ የአብርሃ ጅራ ከተማን ያገኛሉ፤ ከአብርሃ ጅራ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ያለውን 12 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ እንደተጓዙ የግራር ውሃ ቀበሌ ውስጥ የምትገኘውን የግራር ውሃ መንደር ከተማ የምትገኝ ሲሆን ከከተማዋ ደቡብ ምራብ አቅጣጫ በእግር ከሆነ አንድ ስዓት ተኩል (1፡30) ስዓት፤ በመኪና ከሆነ ደግሞ 20 ደቂቃ ከተጓዙ በኋላ የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩን ድንበር ያገኛሉ። እንዲሁም የመተማ ወረዳ ዋና ከተማ ከሆነችው የገንዳ ውሃ ከተማ ከተነሱ ወደ ሽመለ ጋራ መንደር የሚወስደውን መንገድ በመከተል በቁጥር አንድ አልፈው 42 ኪ.ሜ እንደተጓዙ የኮር ሁመር መንደርን ያገኛሉ ከዚም ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በእግር ሁለት ስዓት እንደተጓዙ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩን ያገኛሉ።



ምስል1. የጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ መሰረታዊ ካርታ

አካባቢው በ13^{0}12$^{'}$20.51$^{''}$ እስከ 13^{0}23$^{'}$18.10$^{''}$ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36^{0}13$^{'}$56.73$^{''}$ እስከ በ36^{0}28$^{'}$04.63$^{''}$ ምስራቅ ሎንግቲውድ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታም ከ718 እስከ 1229 ሜትር ይደርሳል። የጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ አካባቢ በስተምስራቅ ከድርማጋ ቀበሌ፤ በስተሰሜን ግራር ውሃና ኮር ሁመር 01 ቀበሌዎች፤ በምዕራብ በመተማ ወረዳ ከሚገኙት መተማ ዮሃንስ (ቁጥር አንድ) እና ዘባጭ ባህር (ሽመለጋራ) ቀበሌዎች እንዲሁም በስተደቡብ ከመተማ ወረዳ ከሚገኙት መሽሃ (አጋም ውሃ)ና ዘባጭ ባህር (ሽመለጋራ) ቀበሌዎች ጋር ይዋሰናል።


1.3.2 የአየር ንብረት

የጎደቤ የተፈጥሮ ደንና አካባቢው ሱዳኖ-ጊኒ ባዮምን በስርዓተ ምህዳር ደረጃም አባሎ ወይባ(*Combretum-Terminalia* Woodland) ስርዓተ-ምህዳርን ይወክላል።

በአካባቢው የሜትሮሎጂ ጣቢያ ባለመኖሩ በትክክል የተወሰደ የዝናብና የሙቀት መጠን መረጃ ባይኖርም ከምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የተገኙ ማስረጃዎች እንደሚያመለክቱት የአካባቢው የሙቀት መጠን ከ38-48 ^{o}c እንደሚደርስ ሲያመለክት የወረዳው የዝናብ መጠን ከ600-1100ሚ.ሜ እንደሚደርስ ያመለክታል። የጎደቤ የተፈጥሮ ደን ዓመታዊ የዝናብ መጠን ምንም እንኳን ከቦታው የዝናብ መጠን መመዝገቢያ ባይኖርም ከተወሰዱ የዲጂታል መረጃዎች 780 ሚ.ሜ ይደርሳል። (http://www.samsamwater.com/ climate/ climatedata.php?lat =12.5107&lng=36.60878&loc=Amhara+%2CEthiopia)

1.3.3 የመሬት አቀማመጥና የአፈር አይነት

የጎደቤ የተፈጥሮ ደንና አካባቢው የመሬት አቀማመጥ 54.52 ከመቶ ሜዳማ፣ 31.87 ከመቶ ተዳፋታምና 13.61 ከመቶ ገደላማ እንደሆነ ከባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ የGIS ክፍል የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ ።



ምስል 2. የጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ የመሬት አቀማመጥ ካርታ

የጎደቤ የተፈጥሮ ደን የአፈር አይነትን ስንመለከት ከአብክመ ባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ የGIS ክፍል የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሰረዱት በዋናነት የአካባቢው ያለው የአፈር አይነት

Eutric nitisols

Chromic Vertisol

Orthic luvisols የተሸፈነ ነው።።

1.4. የጥናቱ ዓላማ

በሰሜን ጎንደር ዞን ምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን የጎደቤ የተፈጥሮ ደን ሱዳኖ ጉኒያን ባዮም (Sudano-Guinean biome) ጥቅጥቅ ያለ ደን እና የተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መስህብ ሃብቶች አቅም የዝርዝር ጥናት በማካሄድ የአካባቢውን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ለማረጋገጥ የሚያስችል መረጃ ማደራጀት ነው፣

1.4.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

በዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት /IUCN/ መስፈርት መሰረት

- የጎደቤ የተፈጥሮ ደን የብዝሃ- ህይወት ሃብት በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳት፣ እጽዋት ዝርያና ክምችት እንዲሁም የተፈጥሮ ገጽታ ይዘት የዝርዝር ጥናት ማካሄድ፣
- የጎደቤ የተፈጥሮ ደንና በአካባቢው የሚገኙ የመስህ ሃብቶችን በመለየት ለቱሪዝም ዕድገት ያላቸውን አቅም ማጥናት፣
- የታሳቢ ጥብቅ ቦታው መቋቋም፣ ለሀገራዊና አካባቢያዊ ልማት የሚኖረውን ሚና ማጥናት፣
- ጉዳዩ የሚመለከታቸው አጋር አካላት ሊኖራቸው የሚችለውን ተግባርና ኃላፊነት በመለየት ወደፊት አካባቢው ወደ ብሄራዊ ፓርክነት ደረጃ ሊመጣ የሚችልበትን ሁኔታ ማመላከት፣
- በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ በወረዳው አጋር አካላት የተከናወነውን የዳር ድንበር መከለል ለብዝሃ ህይዎት ልማትና ጥበቃ በመስፈርቱ መሰረት መሆኑንና በዚህ ክለላ መሰረት ደንብ ማዘጋጀት የሚያስችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

1.5. የጥናቱ ስልቶችና ቁሳቁሶች

1.5.1 ጥቅም ላይ የዋሉ ዋና ዋና ማስፈፀሚያ ስልቶች

- የሚመለከታቸውን አጋር አካላት በመያዝ (አካባቢ ጥበቃ፣መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ፣ግብርና ፣ ሚሊሽያ፣ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች፣ ከአጎራባች ቀበሌዎች የተወከሉ አ/አደሮችን በመያዝ) የጎደቤ የተፈጥሮ ደንና አካባቢው ውስጥ የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ ኢኮሲስተም እና የአካባቢው ብዝሃ ህይወት ሃብት ይዘት ጥናት ተካሂዷል፣
  - የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ ኢኮሲስተምና የሶሽዮ-ኢኮኖሚ ጥናት ለማካሄድ የጥናት የጉዞ መስመሮችን ተጠቅመናል፣
  - የሚመለከታቸውን የዞንና የወረዳ መ/ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን በማነጋገር ሁለተኛ ደረጃ መረጃ ተሰባስቧል ፣
  - በአካባቢው ላይ ከአሁን በፊት የተሰበሰቡና የተጠኑ መረጃዎችን ተጠቅመናል፣
  - የጎደቤ የተፈጥሮ ደንና አካባቢው የተዘጋጁ መረጃዎችን ከኢንተርኔትና ሌላ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ አውለናል፣
  - ዕፅዋት፣ ታላላቅ አጥቢዎችንና አዕዋፍን ለመለየት ጋይዶችን ተጠቅመናል

1.5.2 ለጥናቱ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች

- ጂፒኤስ.....1
- ባይኖኩላር.....1
- ዲጂታል ፎቶ ካሜራ.....1
- ቶፖ ሸት..... (የአካባቢውን ቶፖሸቶች)
- ጋይድ ቡክ.....(የአእዋፍት፣ የአጥቢዎችና የዕፅዋት ማረጋገጫ መጽሐፍት)

1.5.3 የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በወረዳና በዞን ደረጃ ስለጎደቤ የተፈጥሮ ደንና አካባቢው የተለያዩ ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ተሰብስበዋል፣
- በወረዳና በዞን ደረጃ በጎደቤ የተፈጥሮ ደንና አካባቢው ለኢኮ ቱሪዝም ምቹ የሆኑ ባህላዊና ተፈጥሮዊ ቅርሶች ተለይተዋል፣
- በጎደቤ የተፈጥሮ ደንና አካባቢው መረጃ ተሰብስቧል፣
- ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመሆን በጎደቤ የተፈጥሮ ደንና አካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትን፣ ዕፅዋትን፣ ሥርዓተ-ምህዳርና የሶሽዮ- ኢኮኖሚ ሃብቶች አጠቃላይ መረጃዎች ተሰብስበዋል፣
- በአካባቢው እየደረሱ ያሉ ዋና ዋና ተጽዕኖዎች ተለይተዋል፣

2. የጥናቱ ውጤት

2.1 ስለ ተፈጥሮ ደኑ የጥበቃ ስልትና ታሪክ

የጎደቤ የተፈጥሮ ደን ስያሜውን ያገኘው የምዕራብ አርማጭሆ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በ2005 ያደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው አካባቢው ለሱዳን ቅርብ ከመሆኑ የተነሳ ድንበር ጠባቂዎች ተገኛኝተው ስንቅ፣ መረጃና ትጥቅ ይለዋወጡበት የነበረና ጠረፍ ጠባቂዎችም ጠላትን ለመምታት በምሽግነት ይተቀሙበት ስለነበረ ጎደቤ የሚለው ቃል ጎደበ፣መሸገ ወይም ቦታ ያዘ ለማለት እንደሆነ የጥናት ዶኩመንቱ ያሳያል፡፡ የጎደቤ መንደር የተመሰረተበትና የፈለሰበት ትክክለኛ ጊዜው መቼ እንደሆነ ማረጋገጥ ባይቻልም አካባቢውን ለመጠበቅ በ1933 ዓ.ም አካባቢ በዐጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የጎደቤ መንደር መመስረቱንና በኢ.ዲ.ዩና በደርግ መካከል ይደረግ በነበረ ውጊያ መንደሩ መፍለሱን የአካባቢ ነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡ የጎደቤ መንደር በአካባቢው ለመመስረቷ ጎደቤ ወንዝ አካባቢ ይጠቀሙባቸው የነበረ የድንጋይ ወፍጮዎችን ስባሪና የቀብር ቦታዎችን በመስክ በነበርንበት ወቅት በመረጃነት ተመልክተናል፡፡

ምንም እንኳን በአካባቢው ብዙ ሰው ባለመኖሩ በወቅቱ ለደን ጥበቃ ሰው መድቦ ማስጠበቅ አስፈላጊ ባይሆንም አከባቢውን በማልማትና ከድንበር ወራሪዎች ለመጠበቅ ከጎደቤ መንደር በተጨማሪ በአብርሃ ጂራ አከባቢ መንደሮች መኖራቸውንና የአብርሃ ጅራ ሚካኤል ቤተክርስቲያንም በ1963 ዓ.ም ተመስረቶ በአካባቢው በነበረው የጸጥታ ችግር ምክንያት ወደ አብደራፊ መወሰዱንና በኋላም አካባቢው እንደገና ሲለማ ወደ ቦታው መመለሱን የአካባቢ ነዋሪዎች ያስረዳሉ፡፡

ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ እንደገና ሰዎች ወደ አካባቢው ለእርሻ ስራና ለከብት እርባታ ስራ በመስፈራቸውና እንዲሁም በ1990ቹ መንግስት የሰፈራ ፕሮግራምን በመዘርጋቱና የኢንቨስትመንት እርሻዎችን ለባለሃብቶች በመስጠቱ አካባቢው ከተፈጥሯዊ አካባቢነት ይልቅ ወደ ልማት ቦታነት ተቀየረ፡፡ በዚህም ሳቢያ ለጥብቅ ስፍራና ለልማት አካባቢ የሚሆኑ ቦታዎችን መለየት በማስፈለጉ በ2000ዓ/ም የወረዳው አመራር የሰፈራ ኘሮግራም ለማስፈር ቦታው ቢመረጥም በጎደቤ ውስጥ ያለውን ብዝሃ ህይወት ለመጠበቅና ለመከባከብ ሲባል የወረዳው ህዝብና የሚመለከታቸው አካላት ባደረጉት ጥረት የሠፈራ ኘሮግራሙ ተሠረዞ ወደ ሞገሴ ቀበሌ የማስፈር ስራ የተከናውኗል፡፡ ከዚያም በጎደቤ ያለውን ደን እና ብዝሃ ህይወት ግምት ውስጥ በማስገባት በዚሁ ዓመት የወረዳው ምክር ቤት በሙሉ ድምፅ በማፅደቁ ጥብቅ

ደን ሆኖ እንዲቀጥል በመወሰን ለሚመለከታቸዉ አካላት በማስታወቅ ጎደቤ ጥብቅ ደን ሆኖ እንዲጠበቅ ተደርጓል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በ2004 ዓ.ም በአካባቢው በተካሄደው የብሎክ አሰራር ስርዓት የክልል አካባቢጥበቃ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ ከወረዳው የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለብዝሃ ህይወት ልማት እንዲውል ከኢንቨስትመንት ብሎኮች በመለየት የወረዳው ግብርና ጽ/ ቤት እንዲያስጠብቅ የተደረገ ሲሆን የወረዳው ግብርና ጽ/ቤትም ከክልል በተመደበ በጀት 4 ዘበኛዎች በመመደብ በማስጠበቅ ላይ ነው፡፡ የወረዳው ባህል ቱሪዝም ጽ/ቤትም በ2005 ዓ.ም በካሄደው ጥናት መስህብ መሆን እንደሚችል ያረጋገጠ ሲሆን የክልሉ ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ በህዳር ወር 2007 ዓ.ም ቦታውን ባለሙያ በመላክ ያስጠና ሲሆን አሁን ያለበትን ጫና አንድ ዓመት በልበለጠ ጊዜ ውስጥ መፍታት ከተቻለ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ መሆን እንደሚችል ተረጋግጧል፡፡

2.2 የስርዓተ ምህዳር ሁኔታ

የጎደቤ የተፈጥሮ ደንና አካባቢው የ Sudan–Guinea Savanna ባዮም እና *Combretum-Terminalia* Woodland ስርዓተ ምህዳርን የሚወክል ሲሆን የዚህ ስርዓተ ምህዳር መገለጫ የሆኑትን የአባሎ ዝርያዎች (*Combretum molle ,Combretum aculeatum, Combretum adenogonium, Combretum collinum)* የወይባ ዝርያዎች (*Terminalia laxiflora* and *Terminalia* brownii)

- ዋልያ መቀር (*Boswellia papyrifera*)
- ሽመል (*Oxytenanthera abyssinica)*
- ክርክራ (*Anogeissus leiocarpa*)
- ዛና (*Stereospermum kunthianum*)
- *Lannea* spp (*Lannea welwitschii, Lannea fruticosa*)አቅፎ የያዘ ነው :: ይህ ስርዓተ ምህዳር በጋምቤላ ብሄራዊ ፓርክ ፣በባጉሳ ብሄራዊ ፓርክ እንዲሁም በአላጥሽ ብሄራዊ ፓርክ በከፊል የተወከለ ሲሆን የጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ወደ ጥብቅ ስፍራነት ደረጃ ማደግ የበረሃማነት መስፋፋትን እንደመቀነት በመሆን እየተከላከለ የነበረውንና አሁን መቀነቱ የተቋረጠውን የአባሎ-ወይባን /*Combretum-Terminalia* Woodland ስርዓተ ምህዳር የጥበቃ ሽፋን ያሰፈዋል፡፡



ምስል3. የጎደቤ ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ ሰርዓተ ምህዳር

ይህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ለአካቢውና ለታችኛው ተፋሰስ በውኃ ምንጭነት የሚያገለግሉ እንደ ጎደቤ ያሉ ወንዞችን የያዘ ከመሆኑም በተጨማሪ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው መኖር የአካባቢው የከርሰ ምድር ውኃ እንዲበለጽግ ስላስቻለው በአካባቢው ያሉ እንደ ግራር ውሃ ያሉ መንደሮች የተሻለ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት እንዲኖራቸው አስችሏል፡፡

2.3 የዱር እንስሳት

የጎደቤ የተፈጥሮ ደን ከአሁን በፊት ብዙ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት ተጠልለው እንደቆዩበትና እንደ ዝሆን፣ አንበሳ ወደንቢ የመሳሰሉ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት ታሪካዊ የመኖሪያ አካባቢ እንደነበረ የምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በ2005 ዓ.ም አካባቢውን የቱሪስት መዳርሻ ለማድረግ ባደረገው ጥናት ለመጠቆም የሞከረ ቢሆንም ግን አካባቢው እየደረሰበት ባለው አሉታዊ ተጽዕኖ ምክንያት የዱር እንስሳት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመምጣቱ የዱር እንስሳትን በቀላሉ ማየት አዳጋች ሆኗል፡፡

ሆኖም አካባቢው በአግባቡ ጥበቃ ከተደረገለት አሁን ካሉት የዱር እንስሳት ውስጥ የጥበቃ ማዕከል ይሆናል ተብሎ የታሰበው የቆላ አጋዘንን ጨምሮ ሌሎች የዱር እንስሳት በአደንና ሌሎች ችግሮች ምክንያት ቁጥራቸው የተመናመነ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ባለመጥፋቱ ሃብቱን በማልማትና በመጠበቅ ለኢኮ-ቱሪዝም ልማት በግብዓትነት መጠቀም ይቻላል፡፡ በዚህ ጥናት በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ከ21 በላይ አጥቢ የዱር እንስሳትና ከ57 በላይ አዕዋፋት፣ ዝርያዎች እንዳሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በአሁኑ ሰዓት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚታወቁት

ከታላላቅ አጥቢ እንስሳት መካከል:-

- የቆላ አጋዘን (Greater kudu)
- ነብር (Leopard)
- ተራ ቀበሮ (Common/Golden Jackal)
- ድኩላ (Common bushbuck)
- ሚዳቋ (Common duiker)
- ጅብ (Spotted Hyena)
- ዝንጅሮ (Anubis baboon)
- ቀይ ጦጣ (Patas monkey)
- አውጭ (Aardvark)
- ጦጣ (Vervet Monkey) ጥቂቶቹ ናቸው። ለዝርዝር መረጃ ዕዝል ሁለትን ይመልከቱ። በዕዝል ሁለት ከተመለከቱት ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት ውስጥ Aardvark (EN) እና Honey badger (VU) በIUCN የቀይ መዝገብ መጽሃፍ ሰፍረው የሚገኙ በመሆኑና ልዩ ትኩረት የሚሹ በመሆናቸው የዚህ ቦታ እውቅና ማግኘት ዝርያዎችን መጠበቅ ያስችላል።



ምስል 4. የዱር እንስሳት አመላካቾች በጎደቤ

አዕዋፋትን በተመለከተ በኢትዮጵያ ውስጥ 861 የወፍ ዝርያዎች ይገኛሉ:: ከነዚህም ውስጥ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ውስጥ 668 የወፍ ዝርያዎች የሚገኙ ሲሆን በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው እና አካባቢው በጥናቱ ወቅት ከ57 በላይ የወፍ ዝርያዎች መለየት ተችሏል።

በሀገራችን ከሚገኙ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመጥፋት የተቃረቡ (Globally threatened) 31 ዝርያዎች ውስጥ 21 በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ውስጥ ተጠልለው የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ባለ ነጭ ጀርባ የአፍሪካ ጥንብ አንሳ /African white backed Vulture (EN) እና Red-footed Falcon (NT) በአካባቢው ተጠልለው እንደሚኖሩ በጥናቱ ወቅት ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን የተለያዩ በቀለማቸውና በዝማሬያቸው የሚማርኩ የአዕዋፍ ዝርያዎች መገኛም ነው። በአካባቢው የሚገኙ የወፍ ዝርያዎችን ዓይነትና ቁጥር በትክክል ለማወቅ በተለያየ ወቅት

ጥናት ማድረግ የሚያስፈልግ ሲሆን በጥናቱ ወቅት የተገኙ የአፅዋፍ ዝርያዎችን ዕዝል ሶስት ላይ ይመልከቱ፡፡

2.4 የዕፅዋት ሽፋንና ዓይነት

የጎደቤ የተፈጥሮ ደን ከ81 በላይ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎች በጥናት ወቅቱ የተመዘገበበት የተፈጥሮ አካባቢ ነው፡፡ ይህ አካባቢ በዋናነት *Combretum-Terminalia* Woodland ስርዓተምህዳር ዕፅዋትን አቅፎ የያዘ ሲሆን እንደ ዋልያ መቀር፣ ዞቢ፣ ሰርኪን፣ አባሎ፣ ደምበቃ፣ አደንድን፣ ሽመል፣ ክርክራ፣ ጫራ፣ ጉመሮና ሌሎችም ዕፅዋት የሚገኙበት አካባቢ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ 163 የእፅዋት ዝርያዎች ለመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው እና) በIUCN ቀይ መዝገብ ላይ የሰፈሩ (Kerry and Harriet, 1998) ሲሆን ከነዚህም ውስጥ

- ዲዛ *(Adansonia digitata)*
- ዞቢ *(Dalbergia melanoxylon)*
- ሰርኪን *(Diospyros mespiliformis)*
- ጫራ *(Pterocarpus lucens)*
- ሽመል *(Oxytenanthera abyssinica)*
- ዋልያ መቀር (*Boswellia papyrifera*)

በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚገኙ በመሆናቸው፤ ይህ አካባቢ የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደመቀነት ሆኖ በርሃማነት ወደ ሃገራችን እንዳይስፋፋ ሲከላከል የቆየውንና አሁን የተቆረጠውን መቀነት አካባቢ ያጠናክራል፡፡ በተጨማሪ የአየር ንብረት ሚዛን ለውጥን ለመቋቋም የሚደረገውን ጥረት ከመደገፉም ባሻገር ሀገራችን ከካርቦን ንግድ ተጠቃሚ እንድትሆን ያስችላል፡፡ የታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የአየር ንብረት ለወጥን (የከባቢ አየር ሙቀት መጨመር) ለመከላከል የከባቢ አየርን ሙቀት በማመቅ ለውጥ የሚያመጣውን ካርቦን ዳይ አክሳይድ በተክሎች አካል ውስጥ ሰብስቦ በማስቀረት ጉልህ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ ለአላጥሽ ብሄራዊ ፓርክ በተወሰደው የጥናት (Vreugdenhil *et al*, 2012) ቀመር መሰረት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው 75.52 tCO_2e/ha በተክሎች አካል ውስጥ ሊቀር ይችላል፡፡ ስሌቱን መነሻ በማድረግ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ 1.434 $MtCO_2e$ አቅፎ ማስቀረት እንደሚቻል ተረጋግጧል፡፡ ይህም ከኢትዮጵያ ዓመታዊ የካርቦን ልቀት ጋር ሲነጻጸር 0.956 ፐርሰንት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ወደ ካርቦን ገበያ መግባት ቢችል ከ5.736 ሚሊዮን ዶላር ያላነሰ

ገንዘብ ሊያስገኝ ይችላል፡፡ በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ውስጥ የሚገኙና በጥናት የተረጋገጡ የዕፅዋት ዝርያዎችን (ዕዝል አንድ) ላይ ተመልከቱ፡፡

2.5. በታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩ ዙሪያ የሚኖሩ ህዝቦች አኗኗር ሁኔታና የሚያደርሱት ተጽዕኖ

2.5.1.የአካባቢው ነዋሪዎች ሁኔታ

የጎደቤ ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ ቆላማ በሆኑ በምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ 3 ቀበሌዎች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩ አሁን ባለው ተጨባጭ እውነታ የተፈጥሮ ሃብቱ ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም በድንበሩ ዙሪያ ቀበሌዎች ከሚኖረው ህዝብ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የጥናት ቡድኑ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን በማጠናቀር የተፈጥሮ ደኑ ከሚገኝባቸው ከላይ ከተገለጹት 3 ቀበሌዎች በተጨማሪ የታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩ አዋሳኝ የሆኑ በመተማ ወረዳ 3 ቀበሌዎችን ለይቷል፡፡ ይህም ታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩ በአጠቃላይ በ6 ቀበሌ በሚኖሩ ህዝቦች መካከል እንደሚገኝ ያሳየናል፡፡

አሁን ባለበት ነባራዊ ሁኔታ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አዋሳኝ ቀበሌዎች ያለውን የህዝብ ቁጥር ለመተንተን አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም በህጋዊና በህገወጥ ሰፈራ ምክንያት በየጊዜው ቁጥሩ ስለሚጨምር ነው፡፡ በእነዚህ ስፍራዎች በከፍተኛ ፍጥነት የህዝቡ ቁጥር እየጨመረ እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ፤ ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ በዝምድና፣ በጋብቻ፣ በአበልጅ፣ በጡት አባትና ልጅ በሚባሉ የተለያዩ ትስስሮች ከሌሎች አካባቢዎች ሰዎች እየመጡ ስለሚሰፍሩ እንደሆነ ለመረዳት ችለናል፡፡ ከአዋሳኝ ቀበሌዎች ወረዳ ገ/ኢ/ልማት ጽ/ቤቶች ባገኘነው መረጃ መሰረት የ2006ዓ.ም የስድስቱ ቀበሌዎች የህዝብ ብዛት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ1 .በጎደቤ ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ ድንበር ዙሪያ የሚኖረው ህዝብ ብዛት፣

ተቁ	ወረዳ	ቀበሌ	የህዝብ ብዛት፣			
			ወንድ	ሴት	ድምር	%
1.	ምዕ/ አርማጭሆ	ኮር ሁመር 01	1034	1007	2041	*4.02*
2	ምዕ/ አርማጭሆ	ግራር ውኃ	1185	1125	2310	*4.55*
3	ምዕ/ አርማጭሆ	ድርማጋ	911	739	1650	*3.25*
		ንዑስ/ድምር	*3130*	*2871*	*6001*	*11.82*

ተቁ	ወረዳ	ቀበሌ	የህዝብ ብዛት፣			
			ወንድ	ሴት	ድምር	%
4	መተማ	መሻ(አጋም ውኃ)	5845	4360	10205	*20.1*
5	መተማ	ዘባጭ ባህር(ሽመለ ጋራ)	5469	4139	9608	*18.9*
6	መተማ	መተማ ዮሐንስ (ቁጥር1)	12657	12350	25007	*49.2*
		ንኡስ ድምር	*23971*	*20849*	*44820*	*88.18*
		ጠቅላላ ድምር	*27101*	*23720*	*50821*	*100*

ከላይ በተገለጸው መረጃ መሰረት በ6ቱ ቀበሌዎች 27101 ወንድና 23720 ሴቶች በድምሩ 50821 ሰዎች ይኖራሉ፡፡ በአዋሳኝ ቀበሌዎች ከሚኖረው ማህበረሰብ ውስጥ 53.3% የሚሆነው ወንድ ሲሆን አብዛኛው የዚህ የማህበረሰብ ክፍል የአካባቢውን ደን በመጨፍጨፍ በእርሻ ስራ ላይ የተሰማራ ነው፡፡

በዚህ መረጃ መሰረት በታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩ ዙሪያ ከሚኖረው ህዝብ 11.82 በመቶው የሚኖረው ተፈጥሮ ደኑ በሚገኝባቸው የምዕራብ አርማጭሆ 3 ቀበሌዎች ውስጥ ነው፡፡ ይህም በኮር ሁመር01፣ ግራር ውኃና ድርማጋ ቀበሌዎች የሚኖረው ህዝብ ድርሻ እንደ ቅደም ተከተል አቀማመጣቸው 4.02፣ 4.55 እና 3.22 በመቶ ነው፡፡ በታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩ ዙሪያ ከሚኖረው ህዝብ 88.18 በመቶ የሚሆነው በመተማ ወረዳ ስር ባሉ 3 ቀበሌዎች ይኖራሉ፡፡ ይህ መረጃ ታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩን ለመጠበቅና ለማልማት ወደፊት በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ ጎረቤት በሆነው የመተማ ወረዳ የሚገኘው የ3 ቀበሌ ህዝብ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን በግልጽ የሚያመለክት ነው፡፡

የአዋሳኝ ቀበሌዎች የገቢ አማራጮች፡- የአካባቢው ነዋሪ የምግብ ፍጆታውን ለማሟላት እና ለሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች የሚያስፈልገውን ወጪ የሚሸፍነው ከሰብል እርሻና ከቤት እንስሳት እርባታ ነው፡፡ በቡድን ውይይቶችና በሁለተኛ ደረጃ በተሰበሰቡ መረጃዎች መሰረት በታሳቢ ፓርኩ አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎች ከሰብል ልማት፣ ከእንስሳት እርባታ፣ ከንግድ፣ ከማር ምርት፣ ከደን ውጤቶች ሽያጭና ከቀን ስራ ገቢ እንደሚያገኙ ሲገልጹ ነገር ግን በዋናነት የሚተዳደሩት በሰብል ልማትና በእንስሳት እርባታ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ሰብል ልማት፤- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ ሰብል በገቢ ምንጭነቱ በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ሰብል የሚመረተውም ለቤት ፍጆታና ለገበያ እንደሆነ በጥናቱ ወቅት ለማረጋገጥ

ተችሏል። በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ ከሚመረቱ ሰብሎች መካከል ማሽላ፣ ጥጥ፣ ሰሊጥ፣ ዳጉሳ፣ ለውዝና በቆሎ ዋና ዋና ናቸው። ሰሊጥ፣ ጥጥና ለውዝ በዋናነት ለገበያ የሚመረቱ ሰብሎች ሲሆኑ ማሽላ ደግሞ ለፍጆታና ለገበያ ይመረታል።



ምስል5. በጎደቤ ዙሪያ የሚበቅሉ ዋና ዋና ሰብሎች

በጎደቤ ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ አዋሳኝ ቀበሌዎች የሚመረቱ ዋናዋና የሰብል አይነቶችን የ2005/6 በጀት ዓመት ምርታማነት ከምዕራብ አርማጭሆ ግብርና ጽ/ቤት ባገኘነው መረጃ መሰረት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ.2፡ በጎደቤ ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ አዋሳኝ ቀበሌዎች የሚመረቱ ዋናዋና የሰብል አይነቶች ምርታማነት በኩንታል

ተቁ	የሰብል አይነት	የመሬት መጠን በሄ/ር	የተገኘ ምርት በኩ/ል	ምርታማነት በሄ/ር	ሽፋን በ%
1	ሰሊጥ	90791	544746	6	32.09
2	ማሽላ	35429	1062870	30	62.62
3	ጥጥ	4580.75	81000	18	4.772
4	በቆሎ	252	5544	22	0.327
5	ዳጉሳ	65	975	15	0.057
6	በርበሬ	108	2160	20	0.127
7	አተር	1.5	30	20	0.002
8	ለውዝ	3	60	20	0.004
ድምር		**131230.25**	**1697385**		**100**

በታሳቢ ፓርኩ ዙሪያ ከሚገኙ የምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ 3 ቀበሌዎች በ2005/06 የምርት ዘመን ከታረሰ 131230.25 ሄክታር መሬት ላይ 1697385 ኩንታል ምርት በነዋሪው ተመራጭ የሆኑ የሰብል አይነቶችን ማምረት የተቻለ ሲሆን በአካባቢው በዚህ የምርት ዘመን በጠቅላላ

ካመረተው ሰብል ውስጥ 62.62% ማሽላ ነው። ከጠቅላላው የሰብል ምርት 62.62፣ 32.09 እና 4.772 በመቶ የሚሸፍነውን በቅደም ተከተል ማሽላ፣ ሰሊጥ እና ጥጥ በማምረት ይጠቀማል።

በአንፃሩ በአካባቢው የእርሻ ስራ ውስጥ አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ የገቢ ማስገኛ ተክሎች ምርት በአካባቢው ገና ያልተስፋፋ መሆኑን ያስገነዝበናል። ከዚህም በተጨማሪ በአየር ንብረት መዛባትና የአካባቢው አርሶ አደር ደንን እየጨፈጨፈ መሬትን በስፋት የመያዝ አባዜ ውስጥ በመግባቱ የተነሳ ከማሳ ዝግጅትና የሰብል እንክብካቤ ጉድለት ጋር በተያያዘ በመስክ እንደታየው በአቀንጭራና የአድሪ ትል በመሳሰሉት አረምና ተባይ ሰብሎች በመጠቃታቸው ምርታማነታቸው እያሽቆለቆለ እንደሆነም ታዝበናል።

እንስሳት እርባታ፡- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ የሚገኙ የቤት እንስሳት በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚቀመጡ የአካባቢው ህብረተሰብ የገቢ ምንጮች ናቸው። የቤት እንስሳት ሃብት ከሚያስገኘው ተጨማሪ ገቢ በላይ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የኃብትና ክብር መገለጫ ሆኖ በማገልገል ላይ ሲሆን የእንስሳት እርባታውም ሙሉ በሙሉ በልቅ ግጦሽ ላይ የተመሰረተ ነው። በመሆኑም በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አዋሳኝ የሚኖሩ አ/አደሮች ከእነዚህ እንስሳት ጋር ያላቸው ትስስር ከፍተኛ ሲሆን ለእነዚህ እንስሳት ግጦሽ የሚሆን መሬትም በአሁኑ ወቅት በዚሁ በተፈጥሮ ሃብቱ ውስጥ ባለው ቦታ እና ሰብል በተሰበሰበባቸው የእርሻ ማሳዎች ነው።

በእንስሳት እርባታ ዘርፍ ላይ ካለው የመኖ እጥረት በተጨማሪ የእንስሳት በሽታ ከዘርፉ የሚገኘውን ውጤት በከፍተኛ ደረጃ እየጎዳው ይገኛል። በአካባቢው በስፋት የሚከሰቱ የእንስሳት ጤና ችግሮች በሚያደርሱት የጉዳት መጠን ቅደም ተከተል፡-

1. በበግና ፍየል፡- ደስታ መሰል፣ የበግና ፍየል ፈንጣጣና አባሰንጋ
2. በዳልጋ ከብት፡- ጉርብርብ፣ አባሰንጋና አፍተግር(ማዝ) ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ህክምና ከሚያገኙት የማያገኙት ይበልጣሉ።

ከላይ ለተጠቀሱትና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በአዋሳኝ ቀበሌዎች የሚገኙ አርሶ አደሮች፣ በባለሙያዎችና አመራሮች አንዲሁም የወረዳ ባለሙያዎች በእንስሳት እርባታው ዘርፍ ጎልተው የሚታዩ ችግሮችን እንደሚከተለው ያጠቃልሉታል።

1. የአካባቢው ማህበረሰብ በእንስሳት ቁጥር የማመንና ልቅ ግጦሽን ለማስቀረት አስቸጋሪ መሆኑ፣

2. በአካባቢው የሰብል ምርት ዋጋ በመጨመሩ(በተለይም ሰሊጥ) አይገብሬ ቦታዎችና የግጦሽ መሬቶች በመታረሳቸው የመኖ እጥረት መከሰቱ፣
3. የቁም እንስሳት የኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋቱና ለድንበር ዘለል በሽታ መንስኤ መሆኑ፣
4. የእንስሳት በሽታ ቅድመ መከላከል(ክትባት) ለመስጠት የመዳህኒት ማቆያ ፍሪጅ አለመኖር፣
5. በሁሉም ቀበሌዎች የተሟላ የእንስሳት ክሊኒክና ባለሙያ አለመኖር፣
6. የወረዳ ባለሙያው ድጋፍ ለማድረግ የትራንስፖርትና የክህሎት ክፍተት መኖር የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሠንጠረዥ.3፡ የጎደቤ ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ አዋሳኝ ቀበሌዎች የቤት እንስሳት መረጃ

ተ.ቁ	የእንስሳት ዓይነት	አዋሳኝ ቀበሌዎች						ጠቅላላ ድምር
		ኮር ሁመር 01	ግራር ውኃ	ድርማጋ	መሻ	መተማ	ዘባጭ ባህር	
1	የዳ/ከብት	1533	1997	2783	50672	5057	28405	**90447**
1.1	በሬ				12876	194	5253	**18323**
1.2	ላም				16010	2235	8064	**26309**
1.3	ወይፈን				11942	824	5053	**17819**
1.4	ጊደር				7602	617	3409	**11628**
1.5	ጥጃ							
	ተባዕት				1132	674	3000	**4806**
	አንስት				1110	513	3626	**5249**
2	ፍየል	5612	3001	2861	5090	2039	13068	**31671**
3	በግ	2312	1668	1837	107	1020	3303	**10247**
4	አህያ	558	130	356	2133	1248	3828	**8253**
5	በቅሎ				100	0	3	**103**
6	ግመል				1	0	1	**2**
7	ደሮ	7082	453	1845	11781	2218	15232	**38611**
8	በንብ							

ተ.ቁ	የእንስሳት ዓይነት	አዋሳኝ ቀበሌዎች						ጠቅላላ ድምር
		ኮር ሁመር 01	ግራር ውኃ	ድርማጋ	መሻ	መተማ	ዘባጭ ባህር	
	የተሞላ ቀፎ							
8.1	ዘ/ቀፎ				0	63	32	95
8.2	የሽግግር				5	2	1	8
8.3	ባ/ቀፎ				85	139	625	849

ከምዕራብ አርማጭሆና ከመተማ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት በዙሪያው ባሉ 6 ቀበሌዎች 134410 የቤት እንስሳት (ዶሮን ሳይጨምር) እና በመተማ ወረዳ በሚገኙ ቀበሌዎች በንብ መንጋ ተሞሉ 849 ባህላዊ፣ 8 የሽግግርና 95 ዘመናዊ ቀፎዎች ይገኛሉ፡፡

በሌላ በኩልም የቤት እንስሳት ሀብት ክምችት በዝርያ አይነቶች ተለያይቶ ሲታይ ነዋሪው የዳልጋ ከብትና ፍየሎችን ማርባት ቀዳሚ ምርጫው መሆኑ ይታያል፡፡ ሁለቱ ዝርያዎች ከጠቅላላው የቤት እንስሳት 67.29 እና 23.56 በመቶ የሚሆነውን ብዛት ይይዛሉ፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት እንስሳት በተጨማሪ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ ዶሮ በከፍተኛ ደረጃ የሚረባ ሲሆን በገቢ ምንጭነቱ ቀላል የማይባል ድርሻ አለው፡፡

2.5.2.በታሣቢ ጥብቅ ሥፍራው የተፈጥሮ ሃብት ላይ የሚታዩ ጫናዎች/ተጽዕኖዎች

የጎደቤ ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ ከክልል ግብርና ቢሮ በሚመደብ በጀት 4 ዘበኞች እየተቀጠሩ ጥበቃ ለማድረግ ቢሞከርም በልቅ ግጦሽ፣ ህገ ወጥ እርሻ መስፋፋት፣ አግባብነት የጎደለው የደን አጠቃቀም፣ ህገ ወጥ አደን እና የተቀናጀ የጥበቃ ስልት ባለመዘርጋቱ የተነሳ በአሁኑ ሰዓት የተፈጥሮ ሀብቱን ህልውና የሚፈታተኑ እርስ በርሳቸው የተሰናሰሉ ስጋቶችን ተመልክተናል፡፡ ከእነዚህም መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡-

- **ልቅ ግጦሽ፣**

የልቅ ግጦሽ መስፋፋት ለተፈጥሮ ቦታው መጥፋት ቁጥር አንድ መንስኤ ሲሆን በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ተረፈ ምርትን ሰብስቦ ወይም ድርቆሽ በማጠራቀም እንሳሳትን የመቀለብ ልምዱ ሆነ ግንዛቤው የለም፡፡ በአካባቢው ካለው የልቅ ግጦሽ ሥርዓት የተነሳም የቤት እንስሳት

ወደ ደኖቹ እየገቡ የእጽዋት ቡቃያ እንዲጠፋ፣ መሬቱ እንዲጠቀጠቅና እንዲጠብቅ በማድረግ የዛፍ ብቅለትን አግዷል። ይህ ሁኔታም የእጽዋቱን (በተለይም እንደ ሽመልና የጣን ዛፍ አይነቶችን) የመራባትንና እራስን የመተካት ሂደት አቋርጣል። ይህ ችግር የተከሰተው ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አዋሳኝ ወረዳዎች በተጨማሪ ከትግራይ ክልል ሁመራ፣ ወልቃይት፣ ጠገዴና ሽሬ አካባቢ እንዲሁም ከሰሜን ጎንደር ዞን ከጭልጋ፣ ታች አርማጭሆና ጠገዴ ወረዳዎች በሚመጡ ዘላኖች አማካኝነት ሲሆን በክረምት ወራት በአማካይ ከ80000 በላይ የቀንድ ከብቶች መቆሚያ ሆኖ እንደሚከርም ከቦታው ላይ የሚገኘው በረትና ከአካባቢው ነዋሪዎች የተገኘው መረጃ ያስረዳል።

ምስል6. የልቅ ግጦሽ ጫና በጎደቤ



ከላይ ከተጠቀሱት አርሶ አደሮች ውጭ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ዙሪያ የሚኖሩት ባለሃብቶች በርካታ ፍየሎችና የዳልጋ ከብቶችን የሚያሰማሩት ለጥብቅ ቦታነት በተከለለው የተፈጥሮ ሃብት ውስጥ ነው። በዙሪያው ያሉ ለእርሻ ስራ ፈቃድ ያላቸው ኢንቨስተሮች/ባለሃብቶችም ቢሆኑ ልቅ ግጦሽን ማስቆም በሚለው አስተሳሰብ ዙሪያ ያላቸው ግንዛቤ እጅግ በጣም አነስተኛ ነው።

- **የህገ ወጥ እርሻ መስፋፋት**

ከልቅ ግጦሹ ቀጥሎ ለታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የጥፋት መንስኤ የህገ-ወጥ እርሻ እንቅስቃሴ ሲሆን ይህ ተግባር የሚከናወነውም በሞፈር ዘመት አርሶ አደሮች፣ ፊውዳላዊ አስተሳሰብ በተጠናወታቸው የምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ ነዋሪ የሆኑ መሬት የሚያከራዩ ጥቂት አርሶ አደሮች እና በተፈጥሮ ሃብቱ ዙሪያ የሚገኙ ኪራይ ሰብሳቢ ባለሃብቶች አማካይነት ነው። በተለይም በምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ ኮሀመር 01ና ግራር ውኃ ቀበሌዎች አብደረግ የሚባለው አካባቢ እና በመተማ ወረዳ በኩል ደግሞ በተፈጥሮ ሃብቱ ድንበር አካባቢ የሚገኙት ሶስቱም ቀበሌዎች የአጋም ውኃ፣ ታጉር-ሽመለጋራና ቁጥር አንድ ጎጦች በስፋት ይከናወናል። በእነዚህ አካባቢዎች የሚገኙትን የዕጣን ዛፍ፣ የዞቢ፣ ጫራ፣ ሽመልና ሰርኪን የመሳሰሉትን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመጥፋት የተቃረቡ የዛፍ ዝርያዎችን በህገ-ወጥ መንገድ በመመንጠርና በማቃጠል የተፈጥሮ ቦታው ሃምሳ በመቶ የሚሆነው ክፍል ወድሞ ወደ እርሻነት እየተቀየረ ይገኛል።




ምስል7. የህገ ወጥ እርሻ መስፋፋት በጎደቤ አብደረግ ጎጥ አካባቢ

በአጠቃላይ የጎደቤ የተፈጥሮ ደን ክልል ከአሁን በፊት በ2004 ዓ.ም ተከልሎ ዳር ድንበሩ ተለይቶ በውስጡ ህጋዊ ይዞታ ለነበራቸው አርሶ አደሮች ትክ የተሰጣቸው ቢሆንም በአሁኑ ስዓት ህጋዊ ይዞታ በሌላቸው ልዩ ልዩ አካላት ከፍተኛ የሆነ ህገወጥ የእርሻ መስፋፋት እየተከናወነበት አንደሆነና ይህንንም ችግር ለመቅረፍ እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ደካማ እንደነበር በሁሉም አጋር አካላት ዘንድ የጋራ ግንዛቤ ተይዟል።

- **ህገ-ወጥ የደን ጭፍጨፋ፣**

የጎደቤ ተፈጥሮ ደን ለአካባቢው ነዋሪ የአየር ንብረቱ የተስተካከለ እንዲሆን በማድረግ እንደ ሳምባ የሚያገለግል ሲሆን በዙሪያው የሚኖረው ማኅበረሰብ ለመጠጥና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚጠቀመውን የውኃ ሃብት የሚያገኘው ከተፈጥሮ ደኑ ከሚነሱ ወንዞችና ምንጮች ነው።

ይህ የተፈጥሮ ደን በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ ለመጥፋት የተቃረቡ የዕፅዋት ዝርያዎችን የያዘ ሲሆን ሳይንሱን ባልተከተለ የእጣን አመራረት፣ ህገወጥ እርሻን ለማስፋፋት፣ ለቤት መሣሪያ፣ ለማገዶ፣ ለከሰል፣ ለጣውላና ለከብቶች ቀለብ ለመሣሰሉት አገልግሎቶች ለመጠቀም በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በዙሪያው በሚኖሩና ሞፈር ዘመት ስግግብ አርሶ አደሮች እያወደሙት ይገኛል።



ምስል8. የህገ ወጥ ደን ጭፍጨፋና ውጤቱ በጎደቤና አካባቢው

በሀገር ደረጃ በጥቂት ቆላማ አካባቢዎች በሚገኙና ዝርያቸው በመመናመን ላይ ያሉ የአባሎ-ወይባ ስርዓተ ምህዳር (Combretum- *Terminalia* ecosystem) ደን ዛፎችን (እንደ ዞቢ፣ ሰርኪን፣ ሽመልና ሚዛን(ቅኔ መብራት) የመሣሰሉትን እየቆረጡና እያወደሙ መሆኑን ተመልክተናል። በተለይም ደግሞ ዞቢን በመቁረጥ በመኪና እና በአህያ እየጫኑ ወደ ሱዳን የሚያሻግሩ ባለሃብቶችና ግለሰቦች እንዳሉ ከባለሙያዎችና የቀበሌ አመራሮች ጋር ባካሄድናቸው ውይይቶች ለመረዳት ችለናል።

ስለሆነም እነዚህን ዛፎች ከጥፋት ለመታደግ ህገ-ወጥ እርሻን፣ ልቅ ግጦሽንና ሰደድ እሳትን በማስቆም የጎደቤ ተፈጥሮ ደንን ህጋዊ ሰውነት አግኝቶ ወደ ዘላቂ የጥበቃና ቁጥጥር ስርዓት ለማምጣት እንዲቻል የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ከወዲሁ ርብርብ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

- **ህገ-ወጥ አደን፣**

በጎደቤ ተፈጥሮ ደን ውስጥ እርሻ ለማረስ የሚመጡ ሞፈር ዘመት አርሶ አደሮች፣ ከብቶቻቸውን ለመሰማራት ከተለያየ ቦታ የሚመጡ ዘላኖች፣ በዙሪያው የሚኖሩ አርሶ አደሮችና ባለሃብቶች አማካይነት በርካታ የሆነ ህገ-ወጥ አደን ይከናወናል፡፡ የእነዚህ አካላት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ለተለያየ ዓላማ መንቀሳቀስ በዱር እንስሳት የመመገቢያና መኖሪያ ቦታ ላይ ጫና በመፍጠሩ ምክንያት እንዲሰደዱ፣ አንዲታደኑና እንዲጠፉ አድርጓል፡፡

በተለይም በከርከሮ፣ ቆቅ፣ ዝግራ፣ ድኩላ፣ አጋዝን፣ ነብር ወዘተ በመሳሰሉ የዱር እንስሳት ላይ ህገ ወጥ አደን ይፈፀማል፡፡ በሰብል ወቅት በሰውና በዱር እንስሳት በተለይም በዝንጀሮና በከርከሮ መካከል ግጭት ስለሚፈጠር ዝንጀሮን ጨምሮ በከርከሮ ላይ ከፍተኛ አደን እየተፈፀመ ይገኛል፡፡

ለጥናት በሜድንበት ወቅትም ዶሮ የሚበሉ ጭልፊቶችና ድመቶች እንኳ ሳይቀር በጥይት ሲገደሉ የተመለከትን ሲሆን ቀደም ባሉት ዓመታት እንደልብ ሲታዩ የነበሩት በርካታ አጋዝኖች በአሁኑ ስዓት ቁጥራቸው ተመናምኖ ሁለት የሚሆኑ እንዳሉ ቢነገረንም ካለባቸው ጫና የተነሳ ለማየት ብንጓጓም ለማግኘት አልታደልንም፡፡

- **የተቀናጀ የጥበቃ ስልት አለመኖሩ**

በ2004 ዓ.ም በተካሄደው የወረዳው መሬት የብሎክ አሰራር መሰረት የጎደቤ ደን ክልሉ ከተለየ በኋላ ከክልል ግብርና ቢሮ በሚመደብ በጀት 4 ዘበኞች ተቀጥረው እየጠበቁ እንደሆነ ከወረዳው የተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ የሥራ ሂደት ያገኘነው መረጃ ቢያመለክትም በአሁኑ ወቅት ግን በተጠናከረ መልኩ ጥበቃ ስለማይደረግለት ከትግራይ ክልል ከሁመራ፣ ወልቃይት፣ ሽሬና ጠገዴ ወረዳዎች፣ ከሰሜን ጎንደር ዞን ከታች አርማጭሆ፣ መተማ፣ ጭልጋ፣ ጠገዴና ምዕራብ አርማጭሆ ወረዳዎች ነዋሪዎችና በዙሪያው በሚገኙ ባለሃብቶች ህገ-ወጥ እርሻ እንቅስቃሴና የቤት እንስሳት ስምሪት አማካኝነት ቦታው ከፍተኛ የሆነ የደን ጭፍጨፋና የህገወጥ አደን ጫና እየደረሰበት ይገኛል፡፡ ለዚህ ችግር መነሻው ደግሞ ልዩ ልዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ የመተማ

እና የምዕራብ አርማጭሆ ወረዳዎች እንዲሁም የምዕራብ አርማጭሆ ወረዳና በተፈጥሮ ሃብቱ ዙሪያ የሚገኙ ቀበሌዎች መካከል ተቀናጅቶ ያለመስራት እንደሆነ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ባካሄድናቸው ውይይቶች ለመረዳት ችለናል፡፡ ለአብነት ያህልም የምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ ፍትሕ፣ ግብርና፣ አስተዳደርና ጸጥታ እና አካባቢ ጥበቃ መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ጽ/ቤቶች ተደጋግፈው ሃብቱን በመጠበቅና ስነምህዳራዊ ጠቀሜታውን በማሳደግ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ ሲችሉ አንዱ አንዱን በመኮነን እርስ በርሳቸው እየተጠላለፉ ለተፈጥሮ ሃብቱ ውድመት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

በተጨማሪም የምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ አስተዳደርና በተፈጥሮ ሃብቱ ዙሪያ የሚገኙ ቀበሌዎች አጠቃላይ መዋቅር እንዲሁ ተናቦና ተግባብቶ ከመስራት ይልቅ አንዱ የአንዱን እንቅስቃሴ በማስተጓጎል ለተፈጥሮ ሃብቱ የሚደረገውን የጥበቃ ስራ ወደ ኋላ በመጎተት ሃብቱን በአጭር ጊዜ ለማጥፍት በሚደረገው ሂደት ላይ ለአጥፊዎች ተባባሪ በመሆን የራሱ አስተዋጽኦ እያደረገ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ በአጠቃላይ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አዋሳኝ ወረዳዎች የሚኖረው አመራር፣ ባለሙያ፣ ባለሃብትና አርሶ አደር መካከል አሁን የሚታየው እርስ በርስ መወነጃጀልና መጠላለፍ የተፈጥሮ ሃብቱ ባለቤት እንደሌለው ከመጠቆሙም በላይ በቀጣይ በእነዚህ ወረዳዎች የመልካም አስተዳደር ችግር ሊያስከትል እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡

ስለሆነም በቀጣይ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በየደረጃው ጥልቅ ውይይት በማካሄድ መስማማት ከዚያም የመፍትሄ ሀሳብ ማስቀመጥና ይህንን ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይላል፡፡

2.6.የቱሪዝም አቅም ጥናት

የጎደቤ ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ ማራኪ የሆነ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ያለውና በአካባቢው ያለውን ሜዳማ መሬት ከፍ ብሎ በኩራት የሚመለከት የሚመስልና በዙሪያው ያሉትን ቦታዎች ሁሉ ዓይን ማየት እከሚቻለው ድረስ ለማየት ልክ እንደ ደሴት በመሆን ያስቃኛል፡፡ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ከ81 በላይ የዕጽዋት ዝርያዎች፣ ከ21 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት እና ከ57 በላይ የአዕዋፍ ዝርያዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ለመጥፋት የተቃረቡ እንደ ዲዛ፣ የእጣን ዛፍ፣ ሽመል፣ ዞቢ፣ ቋራ የመሳሉት ከእጽዋት ዝርያዎች፤ የቆላ አጋዘንና ነብር የመሳሰሉ ከእንስሳት ዝርያቸው በመመናመን ላይ ያሉና በሀገራችን እንደልብ የማይገኙ የብዝሀ ሕይዎት ሃብቶችም ይገኙበታል፡፡

በመሆኑም አካባቢው በብዝሃ ህይወት ሐብት ክምችቱ ከፍተኛ የምርምር ማዕከልና የቱሪዝም መስህብ ሊሆን ይችላል፡፡ በታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩ ውስጥ ያሉ የተፈጥሮ ሃብቶችን እና በዙሪያው ካሉ የባህርዳር፣ ጎንደር፣ መተማ የቱሪስት መንገድ ተከትሎ ከሚገኙ ኃይማኖታዊ፣ ታሪካዊና የተፈጥሮ ቅርሶች ጋር በማስተሳሰር ወደ ልማት ገብተው የቱሪስት መዳረሻ መሆን ቢችሉ በሚኖረው የቱሪዝም እንቅስቃሴ ምክንያት ለክልሉም ሆነ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ከፍተኛ የሆነ የማኅበረ ኢኮኖሚ አስተዋጾ ማበርከት ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ቅርሶች ውስጥ በከፊል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡-

- **የስናር ታሪካዊ ቦታ**

የስናር ታሪካዊ ቦታ ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ደንበር ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በኮር ሁመር 01 ቀበሌ በኩል የሚገኝ ሲሆን ይህ ቦታ ሀገራችን በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (በዩኒስኮ) በዓለማቀፍ ቅርስነት ካስመዘገበችው የመስቀል በዓል አከባበር ጋር ተያያዥ ታሪክ አለው፡፡ የመስቀል በዓል ለሀገራችን ልዩ የመስህብ ሃብት በመሆን በርካታ ቱሪስቶችን በመሳብ መዋለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ በማድረግ የውጭ ምንዛሬን በመጨመር በኩል ራሱን የቻለ አሰተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡ የመስቀል በዓል አከባበር አሁን ለደረሰበት ዓለማቀፍ ቅርስነት ከመመዝገቡ በፊት የተለያዩ የአከባበር ስርዓቶች የነበሩት ሲሆን እነዚህም የተቀጸል ጽጌ በዓል ወይም የዐፄ መስቀል በዓል እየተባለ መስከረም 10 ቀን የሚከበረው የመስቀል በዓል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የመስቀል በዓል አከባበር መስከረም 17 ቀን በብሔራዊ ደረጃ በልዩ ትኩረት መከበር የተጀመረው ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ግማደ መስቀሉ ወደ ሀገራችን ከገባበት ጊዜ አንስቶ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ አዋጅ እንደሆነ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡

ዳግማዊ ዐፄ ዳዊት በ14ኛው ክፍለ ዘመን ግማደ መስቀሉን ከእስክንድርያ በማምጣት ስናር ላይ ሲደርሱ ንጉሡ ወደ መሀል አገር ሳያሰገቡት በዚሁ ቦታ ከባዝራ በቅሏቸው ላይ ወድቀው ሞተዋል፡፡ ከዚያም ልጃቸው ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ግማደ መስቀሉን ከስናር ወደ መናገሻ ከተማቸው ደብረ ብርሀን በማምጣት ለማስቀመጥ ቢሞክሩም ‹‹መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ አስቀምጥ›› የሚል ህልም ስለታያቸው በተፈጥሮ መስቀለኛ የሆነ ቦታ በሀገሪቱ ሲፈለግ ከቆየ በኋላ በመጨረሻም ወደ ግሸን አምባ በመውሰድ እንዳስቀመጡት በተክለ ጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል በሚለው መጽሐፋቸው ያሰፈሩት ሲሆን በተጨማሪም ወ/ሮ ዘውዴ ገብረ እግዚአብሔር ቅዱስ መስቀል በኢትዮጵያ አርቶዶክስ አስተምህሮ በሚለው መጽሐፋቸው በተመሳሳይ ዘግበውታል፡፡

ምስል፱. የስናር ተራራ ገጽታ



ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ስለግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ በዳግማዊ ዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግስት መግባቱ፣ ንጉሱም ስናር ላይ ስለማረፋቸው እና ስለግማደ መስቀሉ አገባብ ያለውን ታሪክ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት በሚለው መጽሐፋቸው ዲያቆን ዮሐንስ ሰሎሞን በሚከተለው መልኩ ይገልጹታል፡፡

የታላቁ ቁስጠንጢኖስ እናት እሌኒ ንግስት የተባለች ደግ ሴት የክርስቶስን መስቀል መስከረም 17 ቀን በ320 ዓ.ም በእጣን ጢስ ምልክት ቁፋሮ አስጀምራ መጋቢት 10 ቀን አግኝታ በማስወጣት ታላቅ ቤተመቅደስ ጎልጎታ ላይ ሰርታ በክብር አስቀመጠችው ይህ መስቀልም ከዚያ ዕለት ጀምሮ እንደ ፀሐይ እያበራ፣ ድውይ እየፈወሰ፣ አጋንንትን እያባባረረ ልዩ ልዩ ታምራትን እየሠራ ሙት እያስነሳ፣ እውራንን እያበራ ተአምራቱን ቀጠለ፡፡ ይህንንም የፋርስ መንግስት መስቀሉን ማርኮ ፋርስ ወስዶ አስቀመጠው፡፡ በዚህን ጊዜ የኢየሩሳሌም ምእመናን የሮማውን ንጉሥ ሕርቃልን እርዳታ በመጠየቅ እንዲመለስ አድርገው በኢየሩሳሌም ብዙ ዘመን ሲኖር እንደገና ኃያላን ነገሥታት ይህን መስቀል እኔ እወስድ እኔ እወስድ እያሉ ጦርነት ፈጠሩ በዚህን ጊዜ የኢየሩሳሌም፣ የቁስጥንጥንያ፣ የአንጾኪያ፣ የኤፌሶን፣ የአርመኒያ፣ የግሪክ፣ የእስክንድርያ የሃይማኖት መሪዎች በሽምግልና ጠቡን አበረዱት ከዚህም አያይዘው ኢየሩሳሌም የሚገኘውን የክርስቶስን መስቀል ለ4 ከፍለው በእጣ አድርገው በስምምነት ተካፈሉ፡፡ ከሌሎች ነዋየ ቅድሳት ጋር በየአገራቸው ወስደው አስቀመጡት፡፡ የቀኝ እጁ የተቸነከረበት የደረሰው ለአፍሪካ ሲሆን፤ ከታሪካዊ ነዋየ ቅድሳት ጋር በግብፅ የሚገኘው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ተረክቦ ወስዶ በክብር አስቀመጠው፡፡ ይህ ግማደ መስቀል ለብዙ ዘመን በእስክንድርያ ሲኖር ቆይቶ በዐፄ ዳዊት ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ገብቷል፤ ካሉ በኋላ ሰለግማደ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ መግባትም የተለያዩ የታሪክ ምንጮች በመጥቀስ በሚከተለው መልኩ ይገልጹታል፡-

ይህ ግማደ መስቀል ለብዙ ዘመን በእክንድርያ ሲኖር በግብጽ እስላሞች እየበዙ ኃይላቸው እየጠነከረ ሔደ፡፡ በእስክንድርያ የሚኖሩ ክርስቲያኖችንም ለመስቀሉ ክብር አትስገዱ፣

የክርስትናን እምነት አጥፉ፣ ግብር ክፈሉ እያሉ አገዛዝ አጸኑባቸው። በግብጽ የሚኖሩ ክርስቲያኖችም ስለሚደርስባቸው ግፍ አንድ ሆነው መክረው ለኢትዮጵያው ንጉስ ለዳግማዊ ዐፄ ዳዊት እንዲህ የሚል መልዕክት ላኩበት « ንጉስ ሆይ በዚህ በግብፅ ያሉ እስላሞች ለክርስቶስ መስቀል ክብር አትስጡ፣ ክርስትናን አጥፉ፣ ግብር ክፈሉ እያሉ መከራ እያጸኑብን ስለሆነ 10ሺ ወቄት ወርቅ እንሰጥሃለን አስታግስልን» ብለው ጠየቁት። በዚህ መሰረት ዳግማዊ ዐፄ ዳዊት ለሃይማኖቱ ቀንቶ 20ሺ ሠራዊት አስከትሎ ወደ ግብጽ ለመዝመት ሲዘጋጅ በሌላ በኩል ደግሞ የአባይን ውኃ ለመገደብ ሙከራ ያደርግ ጀመር። በዚህ ጊዜ በግብጽ ያሉ እስላሞች ፈሩ። ከዚህ የተነሳ በግብጽ እስላሞች በግብጻዊያን ክርስቲያኖች ላይ ያደርሱት የነበረውን ግፍና መከራ ወዲያው አቆሙት።

የግብጽ ክርስቲያኖችም በዚህ ተደስተው 12ሺ ወቄት ወርቅ ለዳግማዊ ዐፄ ዳዊት ላኩላቸው ንጉሡም መልሰው «እንኳን ደስ ያላችሁ የላካችሁትን ወርቅ ልኬአለሁ የእኔ ዓላማ ወርቅ ፍለጋ አይደለም የክርስቶስ ፍቅር አስገድዶኝ በተቻለኝ መጠን ችግራችሁን አስወግጃለሁ አሁን የምለምናችሁ በአገሬ ኢትዮጵያ ረሃብ ቸነፈር ድርቅ ስለወረደብኝ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎበት የነበረውን መስቀልና የቅዱሳንን አጽም ከሌሎች ነዋየ ቅድሳት ጋር ለበረከት እንድትልኩልኝ» ብለው ላኩባቸው። በእስክንድርያ ያሉ ምእመናን ይህ መልዕክት እንደደረሳቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱና ከኤጲስ ቆጶሳቱ ጋር ውይይት በማድረግ ይህ ንጉሥ ታላቅ ክርስቲያን ነው። ስለዚህ ልቡ ደስ እንዲለው የፈለገውን የጌታችን ግማደ መስቀል ከቅዱሳን አጽምና ከነዋየ ቅድሳቱ ጋር አሁን በመለሰው 12 ወቄት ወርቅ የብርና የነሐስ የወርቅ ሳጥን አዘጋጅተን እንላክለት ብለው ተስማምተው በክብር በሥነ ሥርዓት በሰረገላ በግመል አስጭነው ስናር ድረስ አምጥተው በአስረከቧቸው ጊዜ እያሸበሸቡ በግንባራቸው እየሰገዱ በክብር በደስታ ተቀበሏቸው። እንግዲህ ግማደ መስቀሉ በዐጼ ዳዊት ጊዜ ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ገብቷል። ዐጼ ዳዊትም ስናር ላይ ሲደርሱ ተቀምጠውባት የነበረችው ባዘራ ጥላቸው በድንገት ሞተዋል።

ዐጼ ዳዊት ካረፉ በኋላ የመጨረሻ ልጃቸው ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሲነግሥ ወደ ስናር ሐዶ መስቀሉን ካስመጣ በኋላ በመናገሻ ከተማው ደብረ ብርሃን ላይ ቤተመቅደስ ሰርቶ ለማስቀመጥ ሲደክም በሕልሙ ‹‹መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ ላይ አስቀምጥ›› የሚል ህልም አየ። ንጉሡም መስቀለኛ ቦታ እየፈለገ በኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ እንዲህ ዓይነት ቦታ ለመፈለግ ዞረ። በመጨረሻም በወሎ ክፍለ ሀገር አምባሰል አውራጃ ውስጥ ግሸን ከምትባል ቦታ ደረሰ። በእርግጥም ይህች ቦታ ጥበበኛ ሰው እንደቀረጻት የተዋበች መስቀለኛ ቦታ ሆና ስለተገኘች የልቡ

ስለደረሰለት በዚች አምባ ታላቅ ቤተመንግስት አሰርቶ መስቀሉንና ሌሎች ነዋየ ቅድሳት በየማዕረጋቸው በክብር ቦታ መድቦ አስቀምጧቸው ይላሉ፡፡

የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም

- **የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም አጭር ታሪክ**

የማኅበረ ስላሴ አንድነት ገዳም የሚገኘው በሰሜን ጎንደር ዞን መተማ ወረዳ ሲሆን ከጎንደር ወደ መተማ በሚወስደው የአስፓልት መንገድ 132 ኪሎ ሜትር ላይ ደረቅ አባይ ቀበሌ ሲደርሱ ወደ ግራ በመታጠፍ የጠጠሩን መንገድ በእግር ከሆነ አራት (4፡00) ስዓት፤ በመኪና ከሆነ ደግሞ 40 ደቂቃ ከተጓዙ በኋላ ግዝት በር እየተባለ ከሚጠራው ስፍራ ይደረሳል:: ከዚያም ከ45 ደቂቃ እስከ አንድ ስዓት በባዶ እግር ተጉዘው ይህን ጥንታዊና ታሪካዊውን ገዳም ያገኛሉ፡፡ ገዳሙ ማራኪ በሆነ ተፈጥሯዊ የመሬት አቀማመጥ ባለውና ለዓይን በሚማርክ ጥቅጥቅ ባለ ደን በተሸፈነ ተራራማ ቦታ ላይ የተመሰረተ ሲሆን በኢትዮጵያ ቀደምትና ትልቅ ታሪክ ያለው ገዳም እንደሆነ የታሪክ ድርሳናት ይናገራሉ፡፡

ገዳሙ የተመሰረተው በ4ኛው ክ/ዘመን በአብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግስት በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ዘመን ነው፡፡ ጳጳሱም ከነገሥታቱ ጋር በመሆን በሀገሪቱ የነበረው ድርቅና ረሀብ ተወግዶ የጥጋብና የደስታ ዘመን ስለሆነ ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ከአክሱም ወደ ቋራ ሲጓዙ ቦታው ላይ ላዩ አንድ ታቹ ሦስት የሆነ የብርሃን አምድ ከሰማይ እስከ ምድር ተተክሎ አዩ፡፡ ነገሥታቱም የሚታየው የብርሃን አምድ ምስጢሩ ምንድን ነው በማለት ጳጳሱን ቢጠይቋቸው ከላይ አንድ መሆኑ የአንድነታቸው ከታች ሦስት መሆኑ የሦስትነታቸው ምስጢር ሲሆን ይኸውም የሚያስረዳው የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ነው በማለት በብርሃን አምድ ተተክሎ የነበረውን የምስጢር ትርጓሜ አስረዷቸው፡፡ የብርሃን አምድ የተተከለበት ተራራ ስር ደረሱ ጳጳሱም ይህ ቦታ መንፈሰ እግዚአብሔር የሰፈነበት የተቀደሰ ቦታ ነውና እኛም ጫማችንን አውልቀን ሠራዊቱም ትጥቃቸውን ፈትተው መግባት አለብን ብለው ለነገሥታቱ ነገሯቸው፡፡ ነገሥታቱም ጫማቸውን አውልቀው የሠራዊታቸውንም ትጥቅ አስፈትተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ፡፡ ጫማቸውን ያወለቁበትና ትጥቃቸውን የፈቱበት ቦታ ግዝት በር ተብሎ በመከበር እስከ ዛሬ ድረስ አለ፡፡ ከግዝት በር ውስጥ ጫማ ተጫምቶ ባርኔጣ ደፍቶ ዝናር ታጥቆ ጎራዴ ታጥቆ ከበቅሎ ተቀምጦ የሚገባ የለም፡፡

ከተተከለው የብርሃን አምድ ሲደርሱም መልሶ ተሰውራቸው እነርሱም ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን ለማጠየቅ ሰባት ቀን ሱባዔ ገቡ በሰባተኛው ቀንም የተሰውረው ምስጢር ተገለጸላቸው፡፡ በዚህ

መነሻነትም ማንም እንግዳ ሰው እንደመጣ ወደ ቤተክርስቲያኑ ቅጥር መግባት አይችልም። ግዝት በር ውስጥ ከገባ በኋላ የቤተክርስቲያኑ ቅጥር ለመግባት ቢያንስ ለሰባት ቀናት በገዳሙ ስርዓት መሰረት መቆየት ይጠበቅበታል። ጳጳሱም ከሥላሴ ባገኙት ፈቃድ መሰረት ቦታውን ምቅዋመ ስላሴ በማለት በነገሥታቱ ሰራዊት አማካኝነት ቤተክርስቲያን ሰርተው ባርከው ታቦተ ስላሴን አስገቡበት። በተጨማሪም ለቦታው ጠባቂ መነኩሴ በመሾም ዳሩ እሳት መሀሉ ገነት ይሁን በማለት ለገዳሙ መተዳደሪያ ርስት ጉልት ሰጥተው ወደ አክሱም ከነገስታቱ ጋር ተመልሰዋል። ይህ ገዳም ከዚህ በኋላ ምቅዋመ ሥላሴ የሚለው ስያሜ ቀርቶ መካነ ሥላሴ እየተባለ ሲጠራ እንደነበርና መካነ ሠላሴ የሚለውን ስም ደግሞ ቀይረው ማኅበረ ስላሴ እንዲባል ያደረጉት አፄ ፋሲል መሆናቸውን በገዳሙ የተዘጋጀው መጽሔት ያስረዳል።

ገዳሙ ከተመሰረተ ጀምሮ በተለያየ ጊዜ ሰባት የበቁ ቅዱሳን አባቶች እንደነበሩ ይነገራል፤ ከነዚህም ውስጥ አንዱ ቅዱስ አሁን መታሰቢያቸውን ወይም ዝክራቸውን የካቲት 27 ቀን በየዓመቱ የሚከበርላቸው ጻድቁ አቡነ አምደ ሥላሴ ናቸው። አቡነ አምደ ሥላሴ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ሲሆኑ በገዳሙ የነበሩት በአጼ ሱስንዮስ ዘመን ነው። አጼ ሱስንዮስ የካቶሊክ ሃይማኖትን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆንና ህዝቡም በይፋ አንዲቀበል ካሰወጁ ከ18 ዓመት በኋላ በከባድ ደዌ ተያዙ፤ ከዚህ በሽታም የፈወሷቸው አቡነ አምደ ሥላሴ ናቸው። በተጨማሪም አጼ ሱስንዮስን ካሳመኑ በኋላ ሰኔ 21 ቀን 1624 ዓ.ም ደንቀዝ ላይ ተዋሕዶ (የእስክንድርያ ሃይማኖት) ይመለስ የሮም ካቶሊክ ይፍለስ ፋሲል ይንገስ ብለው አዋጅ በማስነገር የአጼ ሱስንዮስን ልጅ አቤቶ ፋሲልን በእርሳቸው አንጋሽነት(ቀቢነት) አጼ ፋሲል ተብለው በአባታቸው ዙፋን ላይ እንቀመጡ አድርገዋል።

አጼ ፋሲልም የተደረገውን ተዓምራት ሁሉ አይተው ምን ስርዓት እንስራላቸው ብለው መከሩ፤ ካህናቱ ቀጸላውን ከካባው እንደደረበ ከቤተ-መንግስት ይግባ ብለው ስርዓት ሰሩላቸው። ንጉሱም ደጋውን የፈቀዱ እንደሆን ከፍርቃን አስከ ደንገል በር ቆላውን የፈቀዱ እንደሆን ከደንገል በር አስከ ድንድር ይውሰዱ አሏቸው። አቡነ አምደ ሥላሴ ግን ይህስ ለሰራዊትዎ ማደሪያ ይሁን ለእኔስ ከቀድሞ ነገስታት ለገዳሙ መተዳደሪያ የተሰጡኝ አርባ አራት ጉልት ደብር ቦታ ይገድሙልኝ አሏቸው። ንጉሱም በውግዘት ከ44ቱ ጉልት ደብር ውስጥ የገበታ ነጩን የብርሌ ጠጁን፣ የደም ዳኝነት፣ የነፍስ ዳኝነት የውርስ ክብት፣ የሰማንያና የይናፋ ዳኝነት እና ይህን የመሳሰለ ሁሉ ሰጥቸዎታለሁ የገዳሙም ስም ማኅበረ ሥላሴ ተብሎ ይጠራልዎ አላቸው። ይህም ከአጼ ፋሲል ጀምሮ በገዳሙ አገር ሲዳኝበት የነበረው ስርዓት እስከ 1966 ዓ.ም ሲሰራበት ቆይቶ በኢትዮጵያ በመጣው ለውጥ ምክንያት ዳኝነቱም ጉልቱም አንድ ላይ ቀርቷል።

ይህ ታላቅ ገዳም ዛሬም ቢሆን በርካታ የሃይማኖት አባቶችን(ጳጳሳትን) ያፈራ ነው። ለምሳሌ ያህል መምህር ገ/ማርያም (ብጹዕ አቡነ ዮሴፍ)፣ መምህር ሀዋዝ (ብጹዕ አቡነ ሰላማ)፣ መምህር ገ/ሥላሴ (ብጹዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ) በዚህ ገዳም በምናኔና ምንኩስና ይኖሩ የነበሩ ናቸው። ይህ ገዳም የሃይማኖት አባቶችን ብቻ ሳይሆን የሐገር መሪዎችንም ጭምር ያስተማረና ያሳደገ ነው። ይህ ይታወቅ ዘንድም ታላቁና ዝነኛው የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት አፄ ቴዎድሮስ ተምረው ያደጉት ከዚሁ ገዳም ሲሆን መቃብራቸውም በዚሁ ቦታ ይገኛል።

ምስል.10 በማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም ስሚገኙ የመስህብ ሃብቶች በከፊል



የማኅበረ ሥላሴ ገዳም በውስጡ በርካታ ታሪካዊ ቅርሶች የሚገኙበት ከነዚህም መካከል የአፄ ቴወድሮስ መቃብር፣ አፄ ዮሐንስ 4ኛ ያበረከቱት የብራና ታምረ ማርያም፣ በአቡነ አምደ ሥላሴ የተዘጋጀውና ገዳሙ የሚተዳደርበት ስርዓተ አበው መጽሐፍ ወዘተ ዋና ዋናዎቹን መጥቀስ ይቻላል። በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረትም ገዳሙን የሚያስተዳድሩት ሰባት ሹማምንት ይመደባሉ፤ እነርሱም መምህር፣ ገበዝ፣ መጋቢ፣ ዕቃ ቤት፣ ሊቀ ረድዕ፣ ዕጓል መጋቢ እና ሊቀ አበው ይባላሉ። እነዚህ ሹማምንት ማኅበሩን ተመካክረው ያስተዳድራሉ፤ በህርመት ነዋሪ ናቸው ሹመታቸውን ካላስወረዱም አይገድፉም።

ይህ ገዳም ከአብርሃ ወአጽብሀ ጀምሮ ከነገስታቱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ስለነበረው ነገስታቱና መሳፍንቱ ለዚህ ገዳም መጽሐፍና ልዩ ልዩ ቅርሳቅርስ ያበረክቱ ነበር፤ ነገር ግን በተለያየ ጊዜ በገዳሙ ላይ ጥፋት ስለደረሰበት ቅርሶቻችን ጠፍተዋል። ከጥቃት የተረፉትንም ቢሆን በዘመኑ የነበሩ አባቶች ጠላት በመጣ ቁጥር ቅርሶችን ለማሸሸት እና ለትውልድ ለማቆየት ሲሉ ንዋየ ቅድሳቱንና ቅርሱን እንደያዙ በየዋሻው ፈልሰው ቀርተዋል። ገዳሙ በሱዳን በኩል አዋሳኝ ጠረፍ በመሆኑ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ወራሪዎች ጥቃት የተጋለጠ ስለነበር ላለፉት 1656 ዓመታት እንኳ አምስት ጊዜ ጥፋት ደርሶበታል። እነዚህም፡-

1. በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ተሰርቶ የነበረውን ቤተክርስቲያን በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ዮዲት ጉዲት የተባለችው የሀገራችን ወራሪ ቤተክርስቲያኑን አቃጥላ መነኮሳቱን ገድላ

ቅርሱን ዘርፋ ገዳሙን አጥፍታዋለች። ዮዲት ያቃጠለችውን ቤተክርስቲያን በአግብአ ጽዮን ተሰርቷል።

2. በአግብአ ጽዮን የተሰራው ቤተክርስቲያን ግራኝ መሐመድ ወረራ ጠፍቷል። በግራኝ መሐመድ ወረራ የጠፋው ቤተክርስቲያን በአፄ ሰርጸ-ድንግል ተሰርቷል።
3. በአፄ ሰርጸ-ድንግል የተሰራውን ቤተክርስቲያን የሱዳን ደርቡሾች አቃጥለውታል፤ መነኮሳቱንም ገድለዋቸዋል።
4. በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግስት ከ1600-1625 ዓ.ም ሃይማኖት በመፋለሱ ምክንያት በመነኮሳቱ ላይ ጫና በመፈጠሩ አቡነ አምደ ሥላሴን ጨምሮ አባቶች በመሰደዳቸው ገዳሙ ጠፍ ሆኖ ቆይቷል።
5. በአፄ ቴወድሮስ ዘመንም እንግሊዞች የገዳሙን ታሪካዊ ቅርሶች መዝብረው ዘርፈውታል።
6. በተፈሪ መኮነን አልጋ ወራሽነት እቴጌ ዘውዲቱ ከ1909-1922 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተቃጠለውን ቤተክርስቲያን አሰርተው በተጨማሪም ለመነኮሳቱ የሚሆን የውኃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ባለሁለት ክፍል በድንጋይና ኖራ አሰርተዋል። ይህ በንግስት ዘውዲቱ የታነጸው ቤተክርስቲያንና የውኃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ለስምንት ዓመታት አገልግሎት ከሰጠ በኋላ በ1928 ዓ.ም ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜ ገዳሙን በከባድ መሳሪያና በአውሮፕላን ሚያዚያ 13 ቀን አቃጥለውታል። በዚሁ ዓመተ ምሕረት (1928) ሚያዚያ 15 እና ሐምሌ 7 ቀን በድምሩ 28 መነኮሳትን ገድለዋቸዋል። ገዳሙን የደበደቡት አውሮፕላኖችም ወደ መጡበት ሲመለሱ አንደኛው ዋለንታ ሁለተኛው ማርዘነብ ከሚባሉ ከገዳሙ ቅርብ ዕርቀት ቦታዎች ላይ አውሮፕላኖቹ ወድቀዋል።

ከታሪካዊና ኃይማኖታዊ ቅርሶች በተጨማሪም በገዳሙ (ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው) ውስጥ ከ100 በላይ የዕጽዋት ዝርያዎች፣ ከ26 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት እና ከ92 በላይ የአዕዋፍ ዝርያዎች ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል ለመጥፋት የተቃረቡ እንደ ዲዛ፣ የእጣን ዛፍ፣ ሽመል፣ ዞቢ፣ ቋራ የመሳሉት ከእጽዋት ዝርያዎች፤ ጉሬዛ፣ የቆላ አጋዘንና ነብር የመሳሰሉ ከእንስሳት ዝርያቸው በመመናመን ላይ ያሉና በሀገራችን እንደልብ የማይገኙ የብዝሀ ሕይዎት ሃብቶችም ይገኙበታል። በመሆኑም አካባቢው በብዝሃ ህይወት ሐብት ክምችቱ ከፍተኛ የምርምር ማዕከልና የቱሪዝም መስህብ ሊሆን እንደሚችል ለማረጋገጥ ተችሏል።

የማኅበረ ሥላሴ ገዳም በአሁኑ ስዓት በዙሪያው በሚገኙ የአካባቢ ጥበቃ፣ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤቶች የተረጋገጠ 19070 ሄ/ር የሚሸፍን የቆዳ ስፋት ያለው ሲሆን

የአካባቢውን ብዝሀ ሕይዎትና መልከዓ ምድር በትክክል ለመመልከት የሚያግዙ በተፈጥሮ የተዘጋጁ የመመልከቻ ቦታዎች አሉት።

እነዚህ ቦታዎችም በገዳሙ አባቶችም የተለያየ ስያሜ ተሰጠቷቸዋል፦

- **መምህር አምባ፡** አፄ ቴዎድሮስና በርካታ አባቶች የተማሩበት እንዲሁም ገዳሙ በአሁኑ ስዓት የሚገኝበት አካባቢ ነው።
- **የከረከመችና የወርቅ አምባዎች፡** ከገዳሙ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ የሚገኙ ሲሆን በጭልጋ ወረዳ በኩል ያለውንና እስከ መምህር አምባ ድረስ የሚገኘውን አካባቢ ለመመልከት ይረዳሉ።
- **ኩክቢ አምባ፡** በአካባቢው ከሚገኙት ቦታዎች ሁሉ ከፍተኛ የሆነና በአለፋና ቋራ ወረዳዎችና የገዳሙን አብዛኛውን ክፍል ለመመልከት የሚረዳ ነው።
- **የንጉስ አምባ(ተራራ)፡** አፄ ዮሐንስ 4ኛ ወደ መተማ ለውጊያ ሲሄዱ ገዳሙ መጥተው ያሰረፉበትና ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ያበረከቱበት ቦታ ሲሆን በሽመል ውኃ አካባቢ የሚገኘውን አካባቢ ለመመልከት ይረዳል።
- **ጉርማስ አምባ፡** ከገዳሙ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ በመተማ ወረዳ የሚገኙ አዋሳኝ ቀበሌዎችንና በአምባው ዙሪያ የሚገኘውን የገዳሙን ክልል በቀላሉ ለመመልከት ይረዳል።

የገዳሙ ሥርዓተ-አበው

አቡነ አምደ ሥላሴ ገዳሙን ሲመሩ ሥርዓት ሰርተዋል፤ ይኸውም፦

1. ከገዳሙ ግዝት በር ውስጥ
- ደም አይፈስበትም፣ ጠላ አይጠመቅበትም፣ እንጀራ አይጋገርበትም
- ስብ ቅቤ እንዳይገባበት፣ ሴት እንዳይገባበት
- ሴት የቆላችው፣ የፈጨችው፣ የደቆሰችው፣ የጋገረችው ሁሉ እንዳይገባ ብለዋል።
- ቅዳሜና እሁድ መግባት ክልክል ነው፤ ነገር ግን በጻድቁ በዓል፣ የሐምሌ ሥላሴና አስከሬን ለመቅበር መግባት ይፈቀዳል።
2. የላመ የጣመ አይበላበትም የመነኮሳትና መናንያን ምግባቸውም ወደህ አክር ከሚባል የማሽላ ዝርያ የሚዘጋጅ መኮሬታ ነው።

3. በገዳሙ ማንኛውም መናኝ መጋቢን ሳያስፈቅድ ምንም ዓይነት ስራ አይሰራም፡፡ ጥፍሩን ሲቆርጥ ጠጉሩን ሲላጭ ልብሱን ሲያጥብ መጋቢን አስፈቅዶ ነው፡፡
4. በገዳሙ የሚኖር ማንኛውም አካል የገዳሙን መተዳደሪያ ደንብ ቢያፈርስ የገዳሙ አመራሮች (ሹማምንት) ተሰብስበው "ስርዓተ አበው አንሳ" ይሉታል እርሱም "ስርዓተ አበው አንስቻለሁ" ይላል በአበው ስርዓት ለመዳኘት ፈቃደኛ ነኝ እንደ ማለት ነው፡፡ ከዚያም እንደጥፋቱ ውሳኔ ይሰጠውና ከእንጨት በተሰራች ዘውዴ በምትባል ሽንቁር ባላት ግንድ ሁለት እግሩን አስገብቶ ይታሰራል ለብቻው በአንድ ክፍል ውስጥም እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡
5. ማንኛውም መናኝ እስከ መርፌ ድረስ የግል ሃብት የለውም፡፡ ይህ ግዝት ነው፡፡

የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም እንኳን ለመነኮሳቱ ለከብቶችም ቢሆን ስርዓት አላቸው፡፡ ይኸውም ጥዋት ጥጆችን ከእናታቸው ለመለየት ሲፈለግ **ወገን ወገን ወገን** እየተባለ ሲጨበጨብ ከእናታቸው ወደ ኋላ ቀርተው ለብቻቸው ይሰማራሉ እንጅ አብረው ለመሄድ ሩጫ ፍርጥጫ የለም፡፡ እንዲሁም ማታ ላይ ከእናቶቻቸው ጋር ከተገናኙ በኋላ **አጎድ አጎድ አጎድ** ብሎ እረኛው ሲያጨበጭብ ከእናቶቻቸው እየተለዩ ወደ ማደሪያቸው በራሳቸው ጊዜ ይገባሉ፡፡ በተጨማሪም የነበሩበትን ቦታ ሲለቁ **ጉዞ ጉዞ ጉዞ** ሲባሉ ላም ከጥጃዋ ጋር ሳይለያዩ በአንድነት ይጓዛሉ የሚሰፍሩበት ቦታ ሲደርሱም ላም ራሱ (የላሞች ጠባቂ መናኝ/መነኩሴ) **ሰፈር ሰፈር ሰፈር** ሲሉ ሁሉም በአንድነት ይሰበሰቡና ወገን ወገን ወገን ሲባል ላሙም ወደ አንድ ወገን ጥጃውም ወደ አንድ ወገን ይሰማሩና ማታ በዚያች ሰፈር በተባሉባት ቦታ ይገናኛሉ እንጂ መምራት መጎተት የለም ይህ ሥርዓት ዛሬም አለ፡፡

የማኅበረ ሥላሴ ገዳም ከብቶች በአማራ ክልል የሚገኙ ልዩ የእንስሳት ዝርያዎች ሲሆኑ የወተት ላሞችን ዝርያ ለማሻሻልም እንደ ዝርያ ማዕከልነትም ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም የሚመለከተው አካል ሁሉ የእንስሳቱን ዝርያም መጠበቅና መንከባከብ ይኖርበታል፡፡

- **የጉዛራ ቤተመንግስት**

ከባህር ዳር ጎንደር በሚወሰደው የአስፓልት መንገድ ስንጓዝ የጥንት ነጋዴዎች ማረፊያ ከነበረችው የእንፍራንዝ ከተማ ከመድረሳችን በፊት ወደ ቀኝ ስንመለከት ጉዛራን በጉብታው ላይ ጣናን ፊት ለፊቱ እያየ ይገኛል፡፡ ጉዛራ ማለት በግእዝ መሰባሰቢያ ቦታ፣ የጉባኤ ቦታ ማለት ነው፡፡ ከአስፓልቱ የአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ያለው የጉዛራ ቤተመንግሥት የጎንደር

መንግሥት መስራች በሚባሉት በዐፄ ሠርጸ-ድንግል (1556-1589 ዓ.ም) አማካኝነት የተሰራ ነው።

ንጉሡ በቦታው ቤተመንግሥቱን አንዲያንጹ ያደረጓቸው የተለያዩ ምክንያቶች አንዳሏቸው የተለያዩ ተመራማሪዎች የዘገቡ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ወደ ሰሜን የሚሄደው የንግድ መስመር በዚያ የሚያልፍ መሆኑ፤ ጣና ሐይቅ ከፊት ለፊቱ የተንጣለለ መሆኑ፤ አካባቢው ደጋ መሆኑና ከወባ በሽታ ነጻ መኖኑ፤አካባቢው በእህል ምርት የታወቀ መሆኑ፤ ዋናው የወርቅ ገበያ ለነበረው ፋዘግ ቅርብ መሆኑና ሌሎችም ነበሩ።

ቤተ መንግሥቱ የጎንደርን ቤተመንግሥት መልክ ይዞ በጉብታ ላይ የታነጸ ነው። ፎቅና ምድር ቤት የነበረው ይህ ቤተመንግሥት የንጉሡ እልፍኝ፣ የፍርድ አደባባይ፣ የግብር አዳራሽ፣ ማዕድ ቤትና ሌሎችንም ክፍሎች ይዞ ነበር። ቤተመንግሥቱ ከድንጋይና ከእንጨት የተገነባ ሲሆን ከጎንደር ቤተመንግሥት የሰባ ዓመት ቅድሚያ እንዳለው ይነገራል።



ምስል12. የጉባራ ቤተ መንግሥት ክፉቁ ሲታይ

- **ጎንደርና በውስጧ የሚገኙ ገጸ-በረከቶች**

ጎንደር በኢትዮጵያ የመንግሥት ታሪክ ከአክሱምና ላሊበላ ቀጥሎ ትልቁ የመንግሥት ማዕከል ነበረች። በመንግሥት ማዕከልነት የተቆረቆረችው በአፄ ፋሲል (1624-1660 ዓ.ም) ነው። አፄ ፋሲል ከአባታቸው ከአፄ ሱስንዮስ ስልጣን ከተረከቡበት ከ1624 ጀምሮ ለአራት ዓመታት በደንቀዝና አዘዞ አካባቢ ሲያስተዳድሩ ከቆዩ በኋላ ወደ ጎንደር በመምጣት በ1628 ዓ.ም ከተማዋን ቆርቁረዋል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አስከ ጎንደር ዘመን ማክተሚያ ፈፃሜ መንግሥት አፄ ተክለ ጊዮርጊስ (1772-1777) ድረስ የሀገሪቱ ዋና ከተማ በመሆን አገልግላለች።

ጎንደር የመንግሥት ማዕከል ብቻ ሳትሆን በጊዜው የመንፈሳዊ ትምህርት፣ የኪነ ሕንጻ ጥበብና የሌሎች የዕደ ጥበብ ውጤቶች መማሪያና መፈለቂያ ማዕከልም ነበረች። በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የመጻሕፍት እና የአቋቋም ትምህርት ይበልጥ የተስፋፋው በየሀገሩ ያሉ ሊቃውንት በመናገሻ ከተማዋ ጎንደር በነገሥታቱ አማካይነት በመሰባሰባቸው ሲሆን ከዚያን ዘመን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ መንፈሳዊ ትምህርት በስፋት የሚሰጥባት የትምህርት ማዕከል ለመሆን ችላለች።

ምስል 13. የአፄ ፋሲል ቤተመንግስት



በአሁኑ ስዓት በዋና ከተማዋ ከ92 ያላነሱ አብያተ ክርስቲያናት ሲገኙ በአብነት ት/ቤት ረገድም የመጻሕፍት ጉባኤያት፣ የአቋቋም ምስክር፣ የቅኔ አብያተ ጉባኤያት እንዲሁም የዜማ ት/ቤቶች ይገኛሉ።

አፄ ፋሲልና ተከታዮቻቸው የሰሯቸው አብያተመንግስታትና አብያተክርስቲያናት ለከተማዋ ተደናቂነትንና ውበትን አላብሷታል። በጎንደር ከተማ ከሚገኙትና ለከተማዋ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ካሉት የቱሪስት መስህቦች መካከል የአፄ ፋሲል ግቢ፣ የአፄ ፋሲል መዋኛ፣ ራስ ግንብ፣ ደብረብርሃን ሥላሴና ቁስቋም ቤተክርስቲያንና የእቴጌ ምንትዋብ ቤተመንግስትን መጥቀስ ይቻላል።

ከእነዚህም በተጨማሪ ከአፄ ፋሲል ግቢ በሰተሰሜን አቅጣጫ 3 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው ወለቃ ወይም የፈላሻ መንደር እየተባለ የሚጠራውና ከአይሁዶች አመጣጥና ስራ ውጤቶቻቸው ጋር የሚያያዘው ሌላው በከተማዋ የሚገኝ የቱሪዝም የመስህብ ሃብት ነው።

- **የሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ**

የሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ከጥንታዊቷ ጎንደር ከተማ 118 ኪሎ ሜትር ፣ ከደባርቅ ደግሞ 18 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ፓርኩ ከአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ በመቀጠል በ1962 ዓ.ም በሀገር ደረጃ ህጋዊ እውቅና ያገኘ ሲሆን በ1970 ዓ.ም ደግሞ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኒስኮ) በዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ቅርስነት ለመመዝገብ

ችሏል። ፓርኩ ባለው ልዩ የመሬት ገጽታ (መልክዓ ምድር) እና ብርቅየ የዱር እንስሳት ምክንያት በ1970 ዓ.ም በዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ቅርስነት በዩኒስኮ ቢመዘገብም በፓርኩ ላይ ይደርስ በነበረው አሉታዊ ጫና በ1978 ዓ.ም እንደገና በአደገኛ ሁኔታ ላይ ከሚገኙ ቅርሶች ውስጥ (in danger list) መዝግቦታል።

ምስል.14 የሰተሜን ራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ከፊል ገጽታ



ብሔራዊ ፓርኩ እካሁን በተካሄዱ ልዩ ልዩ ጥናቶች መሰረት በውስጡ ከ1200 በላይ የእጽዋት፣ ከ22 በላይ የታላላቅ አጥቢ፣ ከ12 በላይ የታናናሽ አጥቢና ከ180 በላይ ደግሞ የአዕዋፍት ዝርያዎች መጠለያ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥም 20 የእጽዋት፣ 4 የታላላቅ አጥቢዎች፣ 5 የታናናሽ አጥቢዎቻና 6 የአዕዋፋት ዝርያዎች በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅየዎች ናቸው።

በኣትዮጵያ ብቻ ከሚገኙት ብርቅየዎች ውስጥም ዋልያን ጨምሮ ሶስት የእጽዋት ዝርያዎች ደግሞ ከሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ በስተቀር በሌላው የሀገራችን ክፍል የማይገኙ መሆናቸውን ጥናቶች ያስረዳሉ።

- **ድሙህ ኪዳነምሕረት ገዳም**

ድሙህ ኪዳነምሕረት ገዳም ከመተማ ወረዳ ዋና ከተማ ገንዳ ውኃ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በአቸራ ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን ከገዳሙ ለመድረስ 55 ኪሎ ሜትሩን በመኪና ከተጓዙ በኋላ በእግር ደግሞ አንድ ስዓት መጓዝ ይጠይቃል።

ገዳሙ የተመሰረተው በግብጻዊው ጻድቅ አቡነ ቢኒያሚን ሲሆን የምስረታ ጊዜውም በአስራ አንደኛው ክ/ዘመን መጨረሻና በአስራ ሁለተኛው ክ/ዘመን መባቻ አካባቢ እንደሆነ በገዳሙ የሚገኙ አባቶች ይገልጻሉ። በተጨማሪም በገድለ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እንደተጻፈው አቡነ ሳሙኤል ዘደብረ ወገግና አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ በዚህ ቦታ በጾምና ጸሎት ተወስነው በምነና ከቆዩ በኋላ ወደ ምድረ ከብድ ሄደዋል በማለት የቦታውን ታላቅነት ያስረዳሉ።

በነገረ መስቀል መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው ከሆነ ደግሞ አዒ ዘርዓ ያዕቆብ የጌታችን የመዳኅኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል ይዘው ከግብጽ በሱዳን በኩል አድርገው

ሲያልፉ በዚህ ቦታ ማረፋቸውን እና ከዚህ ተነስተው ሲሄዱ ከመስቀሉ ጋር አብሮ የመጣው አክሊለ ሶክ(በጌታ ላይ የአይሁድ ንጉስ ነህ ሲሉ አይሁዶች የደፉበት የሾህ አክሊል) ተረስቶ ቀርቶባቸዋል። ከዚያም ከተወሰነ ጉዞ በኋላ ድማህ (መሀል አናት ማለት ነው) ቀረብን ሲሏቸው ንጉሡም ተውት ፈቃዱ ስለሆነ ነው ማለታቸውንና ከዚህ ንግግር በመነሳት ቦታውን የአካበቢው ሰዎች ድሙህ ብለው እንደጠሩት ይነገራል።

ድሙህ ገዳም እጅግ ማራኪ የሆነ የመሬት አቀማመጥ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከተራራው አናት ላይ ከተወጣ በኋላ ያለው የጸጥታና እና የአርምሞ ድባብ ከሀገር በቀል እጽዋቶችና አዕዋፋት ድምጽ ጋር የፈጠረው መስተጋብር ህሊናን ወደ ማይታወቅ ዓለም ይዞ የመምጠቅ ተጽዕኖው እጅግ ከፍተኛ ነው። ገዳሙ በአሁኑ ስዓት 1050 ሄ/ር መሬት ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በውስጡም ራቁታቸውን ይጓዙ በነበሩ መናኝ ከእየሩሳሌም የመጣ ነው የሚባለውን #አባ ራቁት; የዛፍ ዝርያን ጨምሮ ሌሎች ጥቁር እንጨት፣ ይገኙበታል።

ምስል 15 የድሙህ ኪዳነምሕረት ከፊል ገጽታ



የድሙህ ኪዳነምሕረት ገዳም በአሁኑ ስዓት 22 የሚደርሱ መናኞች የሚኖሩበት ሲሆን በቦታው ላይ የተሰራ ቤተክርስቲያን የለውም። ከአሁን በፊት ቤተክርስቲያን ተሰርቶባቸው የነበሩና በደርቡሽና በጣሊያን ወረራ ጊዜ የጠፉ (የተሰውሩ) የሚካኤል፣ የመድኃኔዓለምና የኪዳነምሕረት አምባዎች እየተባሉ የሚጠሩ ሦስት ቦታዎች ይገኛሉ። በተለይም ደግሞ በኪዳነምሕረት አምባ ላይ በሚደንቅ ሁኔታ የተሰራ የድንጋይ አትሮኑስ የሚገኝ ሲሆን በዚህ አካባቢ ስውራን ባህታዊያን ለጸሎት እደሚጠቀሙበትና የቅዳሴ ድምጽም እንደሚሰማ መናንያን አባቶች ይገልጻሉ።

ገዳሙ በዕቁሪት የሚተዳደር ሲሆን የተጻፈ እንደ ማኅበረ ሥላሴ ዓይነት መተዳደሪያ ደንብ ባይኖረውም በትውፊት የተቀበሉት እና አሁን ድረስ መናንያኑ የሚተዳደሩበት ህገ ደንብ አላቸው። እነዚህም

- ✓ የጥሉላት(የፍስክ) ምግብ አይገባበትም
- ✓ አንስት አይገቡም

- ✓ በዐብይ ጾምና በፍልሰታ ጾም ጾሙ ከተጀመረ በኋላ አይገባም አይወጣም፤ ንግግርም የለም፡፡
- ✓ ቅዳሜና እሁድ መግባትና መውጣት ክልክል ነው፡፡
- ✓ እህል አይዘራበትም(ሰጪጣና ዝንጅብል ብቻ መናንያኑ በሚኖሩበት ጓሮ በመጠኑ ይፈቀዳል)
- ✓ የእርሻ ቦታና የከብት እርባታ የለውም፤ ወዘተ... የሚሉት ይገኙበታል፡፡

- **የአላጥሽ ብሔራዊ ፓርክ**

የአላጥሽ ብሔራዊ ፓርክ ከጥንታዊቷ ጎንደር ከተማ 309 ኪሎ ሜትር ደቡብ ምዕራብ፣ ከገለጉ ደግሞ 25 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ከ309 ኪሎ ሜትሩ ውስጥም 159 ኪ.ሜ. የሚሆነው የአስፓልት ሲሆን ቀሪው ደግሞ የጠጠር መንገድ ነው፡፡ በሌላ በኩል ከባህር ዳር ተነስቶ ወደ አላጥሽ ብሔራዊ ፓርክ ለመድረስ ሁለት አማራጮች ያሉ ሲሆን የመጀመሪያው ከባህር ዳር በጎንደር አዘዞ ያለው ሲሆን ርቀቱም 489 ኪ.ሜ ነው፡፡ ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ ከባህር ዳር በዱርበቴ ገለጉ ያለው ሲሆን ርቀቱም 350 ያህል ነው፡፡

ፓርኩ ከሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ በመቀጠል በ1998 ዓ.ም በአብክመ ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 38/1998 በፓርክነት ተመዝግቧል፡፡ ቦታው ብሔራዊ ፓርክ ሆኖ ከመመዝገቡ በፊት ባለው የተለያዩ የእጽዋትና የዱር እንስሳት ክምችት የተነሳ ጥብቅ ስፍራ መሆን እንደሚገባው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አስበው እንደነበር ታሪክ ይዘክራል፡፡ ይኸውም ንጉሱ ፋሽስት ኢጣሊያ ሀገራችንን በወረረች ጊዜ ጉዳዩን ለዓለም መንግሥታት ለማስረዳት ወደ እንግሊዝ ሀገር ሄደው ሲመለሱ በሱዳን በኩል ተሻግረው ኦሜድላ ከሚባለው አካባቢ ዲዛ በሚባል ዛፍ ውስጥ ለሰባት ቀናት ያህል ተጠልለውበት ቆይተዋል፡፡ ከዚያም በ1970ዎቹ ጀምሮ በጥብቅ ደንነት ተከልሎ እየተጠበቀ ቆይቷል፡፡



ምስል.16 የአላጥሽ ብሔራዊ ፓርክ ከፊል ገጽታ

የፓርኩ ስያሜን በተመለከተ የተለያዩ ሀሳቦችና ትርጓሜዎች እየተነሱ እያከራከሩ ይገኛሉ፤ አላጥሽ ማለት በአረበኛ ደረቅ ወንዝ ማለት ስለሆነ ለገጽታ ግባታው ጥሩ አይደለም ስለዚህ ይቀየርና በአፄ ቴወድሮስ ልጅ ስም አልጣሽ ይባል የሚል አንድ ወገን አለ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አልጣሽ የአፄ ቴወድሮስ ልጅ ሳትሆን የእቴጌ ምንትዋብ ልጅ

(የብርሃን ሰገድ የቋረኛው ኢያሱ እናት) ናት ካሉ በኋላ አላጥሽ የሚለው ስያሜም ለአልጣሽ መታሰቢያ የተሰየመ እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪ የአነጋገር ዘዬ ነው ይላሉ። አልጣሽ ለሚለው ታሪካዊ መነሻም የሚከተለውን ታሪካዊ ማስረጃ ያቀርባሉ። የአድያም ሰገድ ኢያሱ ልጅ የሆኑት አፄ በካፋ ዐሥር ዓመት ነግሠው ከቆዩ በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ወዲያውኑም በንጉሱ ትክ ሰው ማንገስ ግድ ነበርና እቴጌ ምንትዋብ ለመንገሥ ቢያስቡም ንጉሣዊ ዘር የለዎትም ተብለው የዐሥር ዓመቱ ልጃቸው ኢያሱ ነገሠ። እቴጌይቱም በሞግዚትነት ማስተዳደር ጀመሩ። ለመንግስታቸውም ብርሃን ሰገድ ቋረኛ ኢያሱ አስብለው አሠየሙ። እቴጌ ምንትዋብ ከባለቤታቸው ከአፄ በካፋ ሞት በኋላ ኢያሱ ከሚባል ሰው በስውር እየተገናኙ ሦስት ሴት ልጆችን ወለዱ። ሦስቱ ልጆቻቸውም ወለተ እስራኤል፣ አስቴርና አልጣሽ እንደሚባሉ በጎንደር ደብረ ፀሐይ ቁስቋም ማርያም ቤተክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል። ከዚያም ወለተ አስራኤል የጎጃሙን ባላባት ደጃዝማች ዮሴፈቅን አገባች። አስቴርም ራሰ ስሑልን አገባች። አልጣሽ ደግሞ የበጅሮንድ ተክለሐዋርያት ሚስት ሆነች።

ፓርኩ ያለው ለጥ ያለ የመሬት ገጽታ፣ በውስጡ የያዛቸው በመጥፋት ላይ ያሉ የብዝሐ ህይዎት ሃብቶችና በፓርኩ ዙሪያ የሚኖሩ የጉሙዝ፣ የአገውና የአማራ ብሄረሰቦች ባህል የጎብኝዎችን ቀልብ ለመሳብ የሚችሉ ገጸበረከቶቹ ናቸው። በተጨማሪም የሳህል በረሀ ሙቀትን በመከላከል በረሃማነት በሀገራችን እንዳይስፋፋ በአረንጓዴ ዘበኝነት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

እካሁን በብሔራዊ ፓርኩ በተካሄዱ ልዩ ልዩ ጥናቶች መሰረት በውስጡ የሚኖሩ ከ130 በላይ የእጽዋት፣ ከ37 በላይ የአጥቢዎችና ከ204 በላይ ደግሞ የአዕዋፍት ዝርያዎች ተለይተዋል። ከዚህም በተጨማሪ 7 የተሳቢና ተራማጅ ዝርያዎችና 26 የዓሳ ዝርያዎች መጠለያ ሲሆን በተለይም በክልላችን ክፍሎች መገኘት የማይችሉት አንደ አንበሳና ዝሆን ያሉት ታላላቅ አጥቢዎች መኖሪያም ነው።

- **የአፄ ዮሐንስ ሐውልት**

ይህ ሐውልት ከጎንደር ከተማ 182 ኪ.ሜ ርቀት ላይ እንዲሁም የመተማ ወረዳ ዋና ከተማ ከሆነችው ገንዳ ውኃ በስተሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በ20 ኪ.ሜ ርቀት ሱዳን ደንበር ላይ ከተቆረቆረችው መተማ ዮሐንስ ከተማ ክልል ውስጥ ይገኛል።

እዚህ ታሪካዊ ቦታ ላይ ለሀገራቸው ዳር ድንበር መከበር ሲሉ ከድርቡሾች ጋር በነበረው ጦርነት በ1881 ዓ.ም በጀግንነት የተሰውት የንጉሠ ነገሥት አፄ ዮሐንስ ሐውልት ይገኛል። ካሳ ምርጫ በጥር ወር 1864 ዓ.ም (በ1872 እ.ኤ.አ.) አክሱም ላይ አፄ ዮሐንስ 4ኛ በመባል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ በኋላ መተማ ላይ እከተሰውበት ድረስ ኢትዮጵያን አንድ በማድረግ ያስተዳደሩ መሪ ነበሩ። የንጉሡን የጀግንነት ታሪክ ለመዘከርም በቆሰበትና በክብር በተሰውበት ቦታ ላይ የመታሰቢያ ሐውልት ተሰርቶላቸዋል።

- **ውናኒያ ልዩ የተፈጥሮ መስህብ**

ይህን ማራኪ የተፈጥሮ መልክዓ ምድር በሰሜን ጎንደር ባህልና ቱሪዝም መምሪያ የተዘጋጀው የሰሜን ጎንደር ዞን የቱሪስት መስህቦት በከፊል የሚለው መጽሔት በሚከተለው መልኩ ይገልጸዋል፡-

ውናኒያ ከጎንደር ከተማ 22 ኪ.ሜትር ላይ በምትገኘው የላይ አርማጭሆ ወረዳ በችራ አምበዞ ቀበሌ ውስጥ ከባህር ጠለል በላይ 3000 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል።

ወደዚህ ውብ የተፈጥሮ ስፍራ ለማቅናት ሁለት አማራጭ መንገዶች ያለዎት ሲሆን አንደኛው የወረዳው መዲና ከሆነችው የትክል ድንጋይ ከተማ በመነሳት የ 3 ስዓታት የእግር ጉዞ ማድረግን ሲጠይቅ ሌላኛውና ተመራጩ ደግሞ ከጎንደር ከተማ በመነሳት ወደ ወገራ መስመር 20 ኪ.ሜትር መኪና ጉዞ ካደረጉ በኋላ ለ15 ደቂቃ በእግር አቆራርጠው የሚያደርጉት ጉዞ ነው።

ይህ ተፈጥሮ ሙሉ ለሙሉ ውበቷን የለገሰችው ልዩ የመስህብ ሀብት ከአምባው ላይ ሁነው ሲመለከቱት የጋራው ሸንተረር፣ ግራና ቀኝ የሚገኘው ደን እንዲሁም ደኑንና ጋራውን ለሁለት ከፍሎ መሀል ለመሀል የሚያልፈው የአቋኛ ወንዝ ከአራዊቶችና ከአዕዋፋት ድምጽ ጋር ተደማምሮ ቦታውን ሲመለከቱ ሕይወትዎ በደስታና ፍስሐ ይሞላል። በደኑ ውስጥ በብዛት የሚገኙትን ጭላዳ ዝንጀሮ፣ ጉሬዛና ልዩ ልዩ አእዋፋትን እንደልብ ለመመልከት እንደሚያስችልም ያብራራል።

3. የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ የሚኖረው ጠቀሜታ

ሀ/ ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ

- ሰዎች ከተፈጥሮ ሃብቱ በዘላቂነት መጠቀም የሚችሉበትንና ሰዎችና ተፈጥሮ ተጋግዘው በዘላቂነት የሚቀጥሉበትን ሁኔታ ይፈጥራል፣
- በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል ፣
- የበረሃማነት መስፋፋት ለመከላከል ያስችላል፡፡
- የአየር ንብረት ተፅዕኖዎችን ለመቋቋም ያስችላል፡፡
- በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ውስጥ ያለው ብዝሃ ህይወት ሳይጠፋ እንዲኖር ያስችላል
- በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በአይነትም ሆነ በብዛት ይጠበቃሉ ፣ በተለይም በዓለም ላይ ለመጥፋት የተቃረቡ የእጽዋት ዝርያዎች እንደ ዲዛ፣ዞቢ ፣ጫሪያ እና ሰርኪን የመሳሰሉ እጽዋትንና ሌሎችን የዱር እንስሳት የዘቦታ ጥበቃ (insitu conservation) ማድረግ ያስችላል፣
- የተስተካከለ የውሃ ሃብት ፍሰት እንዲኖር በማድረግ የአካባቢው ህብረተሰብ ዘላቂ የሆነ የውሃ አቅርቦት እንዲኖር ያስችላል፣

ለ/ ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ

- ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ከጐብኝዎች ጋር ተያይዞ ከቱሪዝም አማራጭ በመሆን ለአካባቢው ማህበረሰብና ለመንግስት ገቢ ያስገኛል፣
- ከምርምርና ሣይንሳዊ ጥናት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የአካባቢውን ገቢና አቅም ያጐለብታል፣
- ከታሰቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥና አካባቢዎች የሚነሱ ወንዞች አቅም ስለሚጎለብት በአጎራባች ቀበሌዎች ያሉ ዎንዞች በመስኖ የማልማት አቅም ስለሚጨምር ምርትና ምርታማነት ይጨምራል

ሐ/ ማህበራዊ ጠቀሜታ

- ዓለማቀፋዊና ማህበረሰባዊ የሆኑ ጠቃሚ የባህልና ልምድ ልውውጥ ይኖራል፣
- የአካባቢው ማህበረሰብ የተፈጥሮ ሃብቱን ለመጠበቅም ሆነ በአገባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ዘላቂ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም እንዲኖር ያስችላል፡፡

መ/ሳይንሳዊ ጠቀሜታ

- የዱር እንስሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈተሮአዊ አኗኗራቸው ለሚደረግ ምርምር በማዕከልነት ያገለግላል። በተለይም የጎንደር ዩኒቨርስቲ በቅርብ ርቀት ስለሚገኝ ቦታው ህይወታዊ ላብራቶሪ በመሆን ሊያገለግል ይችላል።
- የባህላዊ መድሃኒቶችን ደህንነት በመጠበቅና በመንከባከብ ጥቅም ላይ በማዋል ሣይንሳዊ ጥናትንም ለማካሄድ ይረዳል።
- በመጥፋት ላይ ላሉ የዱር እንስሳትና እጽዋት ሳይንሳዊ ምርምር ለማድረግ ያስችላል።

መ/ የተፈጥሯዊነት ጠቀሜታ

- ተፈጥሯዊነትን ጠብቆ ለመቆየት ያስችላል። በውስጡ ያሉትን ብዝሃ ህይወትና ሌሎች (አፈር፤ዉሃና የመሬት አቀማማጥ) በተፈጥሮአዊ ገጽታቸው ቆይተው ዘለቂታ ባለው መልክ ጥቅም እንዲሰጡና ተፈጥሮአዊ ይዘታቸው እንዳይጓደል ይረዳል።
- የቆላማውን አካባቢ የእፅዋት ለመጠበቅ ወሳይ ናሙና በመሆን ያገለግላል።

ሠ/ የመስህብነት ጠቀሜታ

- ወረዳው በቅርብ ጊዜ የለማ ከመሆኑ አንጻር በወረዳው ዋና መስህብ ከመሆኑ ባሻገር አካባቢው አጼ ዳዊት የጌታችን ግማደ መስቀል ከእስክንድሪያ ይዘው ሲመለሱ ህይዎታቸው ያለፈው ከዚሁ ከታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ድንበር ከሆነው ከስናር ተራራ ሲሆን አካባቢው የሰው ልጅን ቀልብ ሊገዙ የሚችሉ ማራኪ ገጽታዎች አካቶ የያዘ በመሆኑ የመስህብነት ጠቀሜታው የጎላ ነው።

4. **ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች**

ሀ/ ወካይነት /representativeness/

- ቦታው ሱዳኖ-ጊኒ ባዮምንና በስርዓተ ምህዳር ደረጃም *Combretum-Terminalia* Woodland ስረዓተምህዳር የሚወክል ስለሆነ ቦታው በብሄራዊ ፓርክነት ቢከለል የሰሜን ምዕራብ አማራ የልማት ቀጠና እና በክልላችን ቆላማው አካባቢ የአላጥሸና የባጉሳ ብሄራዊ ፓርኮች ሲኖሩ ይህን የልማት ቀጠናና ስርዓተ ምህዳር የሚወክል የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም የተከለለ ሲሆን የጎደቤ ታሳቢ ፓርክ መከለል የቀጠናውን የጥበቃ ሽፋን ያሰፋዋል።

ከስርዓተምህዳር ውክልና በተጨማሪ በክልላችን ውስጥ ባሉ ጥብቅ ስፍራዎች ጥበቃ ያልተደረገለትን የደምበቃ ዛፍ ለመጠበቅ የሚያስችል ሲሆን *Kigelia africana* / አደንድንን/ ለመጠበቅ የሚያስችል አካባቢ ነው ።

ለ/ የብዛ-ህይወት ክምችት / Diversity/

- የአካባቢውን የብዝሃ-ህይወት ሃብት ስንመለከት የቆላማ አካባቢ እፅዋትን አካቶ የያዘ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ጫሪያ፣ ወንበላ፣ ሽመል፣ ዋልያ መቀር፣ ዞቢ፣ ክርክራ፣ ደምበቃና የመሳሰሉ ዕፅዋትን አቅፎ የያዘ ሲሆን በአካባቢው ሊጠፉ የተቃረበውን የቆላ አጋዘን መጠበቅ ከማስቻሉ በተጨማሪ ባለ ህብረ ዜማና በለህብረ ቀለማት አዕዋፍት በብዛት የሚኖሩበት ቦታ ስለሆነ አካባቢውን በብሄራዊ ፓርክነት መጠበቅ ጠቀሜታው በጣም የጎላ ነው።
- አካባቢው ዙሪያውን በባለሃብቶች እርሻ የተከበበ በመሆኑ እንደ ደሴት በመሆን የብዝሃ-ህይወትንና ስርዓተ-ምህዳርን የያዘ በመሆኑ አካባቢውን መጠበቅ የብዘሃ ህይወት ጥበቃ ማዕከል በመሆን ያገለግላል።

ሐ/ ልዩ መገለጫ / Distinctiveness/

ከ20 አመት በፊት በጎደቤ ዙሪያ ያሉ አካባቢዎች ተፈጥሯዊነቱን እንደጠበቀ የነበረ ሲሆን አሁን ግን አካባቢው በኢንቨስትመንት እርሻ የተከበበ በመሆኑ አካባቢው እንደደሴት በመሆን የተፈጥሮ አካባቢዎች ወካይ ነው።

መ/ ኢኮሎጂያዊ ጠቀሚታ /Ecological importance/

- በታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥና በአካባቢው ያለው አባሎ-ወይባ /*Combretum-Terminalia* Woodland/ ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል
- በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል ፣
- የበረሃማነት መስፋፋት ለመከላከል ያስችላል።
- የአየር ንብረት ተፅዕኖዎችን ለመቋቋም ያስችላል።
- በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ውስጥ ያለው ብዝሃ ህይወት ሳይጠፉ እንዲኖር፡ያስችላል
- የዱር እንስሳት በአይነትም ሆነ በብዛት በተፈጥሮአዊ አኗኗራቸዉ ይጠበቃሉ፣

- የተስተካከለ የውሃ ሃብት በተፋሰሱ በተፈለገው ሁኔታ እንዲኖር ያስችላል

ሠ/ በአካባቢው ላይ ያለ ጫና መጠን /Degree of interference/

- ከባድ የሆነ ልቅ ግጦሽ መኖር
- ሰደድ እሳትና ደን ቃጠሎ
- ለሰሊጥ እርሻ ለማዋል ደን መመንጠርና የሰሊጥ እርሻ መስፋፋት
- የዱር እንስሳት አደን (ለሰው ምግብነት የሚውሉ የዱር እንስሳት ከመጠን በላይ መታደናቸው)

ረ/ የአካባቢው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ /Scientific and monitoring uses/

- የዱር እንሰሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈተሮአዊ አኗኗራቸዉ ለሚደረግ ምርምር በማእከልነት ያገለግላል፡፡ በተለይም የጎንደር ዩኒቨርስቲ በቅርብ ርቀት ስለሚገኝ ቦታው ህይወታዊ ላብራቶሪ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡
- ለአካባቢ ክትትል በሚኖረው ጠቀሜታ የተፈጥሮ ሚዛን ለውጥን መለካት ያስችላል፡፡
- የዱር እፅዋት ናሙናና ተፈጥሯዊ እድገትንና በሰዎች ጣልቃ ገብነት የሚመጣውን ለውጥ ለመለየት ይረዳል፡፡

ሰ/ የቦታ ስፋት /area size/

አንድን ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ በጥብቅ ስፍራነት ተመዝግቦ በውስጡ ያሉትን የተፈጥሮ ሃብቶች ለመያዝ ቢያንስ አንድ ሽህ ሄክታር ሊኖረው ይገባል የሚለውን የ IUCN መስፈርት የሚያሟላና 18987 ሄ/ር በላይ ስፋት ያለው ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በመሆኑ ዝቅተኛ መስፈርቱን ስለሚያሟላ በብሄራዊ ፓርክነት መጠበቅ ቢቻል ለማሳካት የተፈለገውን የብዝሃ ህይዎት ጥበቃና ኢኮ-ቱሪዝም ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡

ሸ/ ቅርፅ /መጠነ ዙሪያ /shape/

ጥብቅ ስፍራዎች በሚቋቋሙበት ወቅት በተቻለ መጠን ዝቅተኛ መጠነ ዙሪያ እንዲኖራቸው ይጠበቃል ፡፡ነገር ግን የአካባቢው መጠነ ዙሪያ ረጅም ቢሆንን ሊያካክስ የሚችል ስፋት ከአካባቢው በአንጻራዊነት ስላለውታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን ወደ ብሄራዊ ፓርክነት ደረጃ በማሳደግ የጥበቃ ሽፋን እንዲያገኝ ያስችላል፡፡

ቀ/ በውስጡ የሚገኙ ብርቅየና ድንቅየ ዝርያዎች /Endemicity/

ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ምንም እንኳን በውስጡ ብርቅየ ዝርያዎችን አቅፎ ባይዝም ከአዕዋፍ ዝርያዎች ውስጥ ለመጥፋት የተቃረቡት

- African white backed Vulture (EN)
- Red-footed Falcon (NT)

***እንዲሁም* ከዕፅዋት ዝረያዎች ውስጥ ለመጥፋት የጠቃረቡትንና ልዩ ጥበቃ የሚያሻቸውን**

- **ዲዛ** *(Adansonia digitata)*
- **ዞባ** *(Dalbergia melanoxylon)*
- **ሰርኪን** *(Diospyros mespiliformis)*
- **ጫራ** *(Pterocarpus lucens)*
- **ዋልያ መቀር** (*Boswellia papyrifera*)
- **ሽመል** *(Oxytenanthera abyssinica* **አቅፎ የያዘ በመሆኑ የቦታውን መከለልና መጠበቅ አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡**

ከሀ-ቀ ያሉትን መስፈርቶች ስንመለከት የጎደቤ የተፈጥሮ ደን ብሄራዊ ፓርክ መሆን የሚያስችለው አቅም ሲኖረው የዳርድንበር ክለላ ስራው ከወረዳው አጋር አካላት ጋር በመሆን የወረዳው አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ያከናወነ ቢሆንም የተያዙ የክለላ መረጃዎች ህጋዊ እወቅና ለማስጠት በቂ ባለመሆናቸው የክለላ ስራውና የጉልት መረጃዎች በጋራ በተስማማነው መሰረት በወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት አስተባባሪነት ተጠቃሎ ለባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ሊላክ ይገባል፡፡

5. የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ጠቀሜታና ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች ጥምረት ዝምድና

የጎደቤ የተፈጥሮ ደንና አካባቢው የብዝሃህይዎት ሃብትን ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ከተጠበቀና ጥቅም ላይ ከዋለ አካባቢያዊ፤ አገራዊና ዓለማቀፋዊ አስተዋፅዖ ጥቅም መስጠት ይችላል፡፡ በተለይም ያለው የተፈጥሮ ሽፋንና መልክዓምድራዊ አቀማመጥ የብዝሃ ህይዎትና ተፈጥሮአዊ ገፅታ ከመጠበቅ አልፎ የዓለም ሙቀትንና የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ የጎላ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ የተፈጥሮ ደኑ የሚሰጠው ጠቀሜታ ከIUCN ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባቸው መስፈርቶች ጋር ሲነፃፀር ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅሙን ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ በታች የተቀመጠዉ ሰንጠረዥ ያለዉ የተፈጥሮ ሀብትና የሚሰጠውን ጠቀሜታ

ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅሙን በማነፃፀር ሊጠበቅ የሚገባዉን ደረጃ ለመወሰን ያስችላል፡፡ ጥብቅ ስፍራ የመሆን መመዘኛዎችን ድምር ውጤት 87.05% ሲሆን አንድ ጥብቅ ስፍራ የታለመለትን አላማ 75% እና ከዚያ በላይ ማሳካት ይገባዋል፡፡ በመሆኑም ከተገኘው የጥናት ውጤት እና ቦታው በርሃማነትን በመከላከል፣ ብዝሃ ህይወትን ከመጠበቅና ለቱሪዝም አገልግሎት ከሚሰጠው ጠቀሜታ አኳያ ብሄራዊ ፓርክ ሆኖ ቢጠበቅ

ሠንጠረዥ 3. የጎደቤ ታሳቢጥብቅ ስፍራ ጠቀሜታና ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም መመዘኛ መስፈርቶች ንፅፅር

አቅም / ጠቀሜታ	ወካይነት	ብዝሃ ህይወት	ልዩ መገለጫ	ኢኮሎጂያዊ ጠቀሚታ	በአካባቢው ላይ ያለ ጫና መጠን	የአካባቢው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ	የቦታ ስፋት/	ቅርፅ /መጠነ ዙሪያ/	ብርቅየና ድንቅየ ዝርያዎች	ደረጃ በ%
ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	ከ	ከ	ዝ	ዝ	66.7
የተፈጥሯዊነት ጠቀሜታ	ከ	ከ	ዝ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	88.9
ኢኮኖሚዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	ከ	ከ	ከ	ዝ	77.8
ማህበራዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	ከ	ከ	ከ	ዝ	77.8
ሳይንሳዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	100
የመስህብነት ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	88.9
ደረጃ በ%	100	100	83.3	100	50	100	100	83.3	33.3	83.32

መፍቻ ከ፡- ከፍተኛ 1-2 ችግሮችና የማያሟላቸዉ ነጥቦች ካሉ

ዝ፡- ዝቅተኛ ከሁለት በላይ ችግሮችና የማያሟላቸዉ ነጥቦች ካሉ

አንድ የተፈጥሮ አካባቢ በየትኛው የጥብቅ ስፍራ ደረጃ (protected area category) እንደሚመደብ ለመወሰን አካባቢው ጥብቅ ስፍራ ቢሆን ማሳካት ያለበትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎችን (Primary management objectives) በመለየትና በማወቅ መሆን ይኖርበታል፡፡ ሠንጠረዥ (6) ላይ ማየት እንደሚቻለው የተፈጥሮ አካባቢው በደረጃ II (protected area category II) መሰረት ጥብቅ ስፍራ ቢሆን በተራ ቁጥር1፣ 3፣4 ፣6 እና 7 የተቀመጡትን የመጀመሪያ ደረጃ

ዓላማዎች የሚያሳካ ይሆናል። ስለዚህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን የብሄራዊ ፓርክነት ደረጃ ተሰጥቶት ማቋቋም ይቻላል። ይሁን እንጅ ቦታው አንድ አመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የክለላ ስራው ተጠናቆ ወዲያውኑ ህጋዊ እውቅና መስጠት ካልተቻለ አሁን ካለበት ህገወጥ እርሻና ልቅ የግጦሽ ስርዓት የጠሰጠውን ደረጃ ሊይዝ ስለማይችል ሁሉም ባለድርሻ አካላት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በአሁኑ ወቅት ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎችን ለመፍታትና ክለላውን በአፋጣኝ ለማጠቃለል የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት እና ቦታው ህጋዊ ዕውቅና እስኪያገኝ ድረስ በአግባቡ ማስጠበቅ ይገባቸዋል። ስለዚህ በተፈጥሮ አካባቢው ላይ እየተፈፀሙ ያሉ ችግሮችን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ እስከተቻለ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚከተሉትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎች (Primary management objectives) የሚያሳካ ይሆናል።

ለብዝሃ ህይወትና ስርዓተ ምህዳር ጥበቃ

የጎደቤ የተፈጥሮ ደን ሱዳኖ-ጊኒ ባዮምን የሚወክል ሲሆን በአባሎ-ወይባ /*Combretum-Terminalia* Woodland ስርዓተ ምህዳር ውስጥ የሚገኙትን የዲዛ፣ ዞቢ፣ ሰርኪን፣ ጫራና ሽመል የመሳሰሉት ዕፅዋትን እንዲሁም በአካባቢው ለመጥፋት የተቃረበውን የቆላ አጋዘን መጠበቅ ያስችላል። ይህን አካባቢ በብሄራዊ ፓርክነት መጠበቅ በአባሎ-ወይባ /*Combretum-Terminalia* Woodland ስርዓተ ምህዳር ውስጥ በሚገኘው የብዝሃ ህይወት ሃብት ልማትና ጥበቃ ለማካሄድ የሚያስችል የዕጽዋትና እንሰሳት ስብጥር በማልማትና በመጠበቅ ለተተኪ ትውልድ ማስተላለፍ ያስችላል።

ሠንጠረዥ.4 Matrix for protected area categories and Management objectives (IUCN, 1994)

		IUCN protected area categories							Total (%)
		Ia	Ib	II	III	IV	V	VI	
No.	Management categories	Strict natural reserve	Wilderness area	National Park	Natural Monument	Habitat/Species Management Area	Protected Landscape/Seascape	Managed Resource Protected Area	
1	Scientific research	√	√	√	√	√	√	√	
2	Wilderness protection	0	0	0	0	0	0	0	

No.	Management categories	IUCN protected area categories							Total (%)
		Ia	Ib	II	III	IV	V	VI	
		Strict natural reserve	Wilderness area	National Park	Natural Monument	Habitat/Species Management Area	Protected Landscape/Seascape	Managed Resource Protected Area	
3	Preservation of species and genetic diversity	0	0	√	√	√	√	√	
4	Maintenance of environmental services	0	0	√	√	√	√	√	
5	Protection of species, natural /culture features	0	0	√	√	√	√	√	
6	Tourism and recreation	0	0	√	√	√	√	√	
7	Education	0	0	√	√	√	√	√	
8	Sustainable use of resources from natural ecosystems	0	0	0	0	0	0	0	
9	Maintenance of natural/cultural/traditional attributes	0	0	0	0	0			
	Total	1	1	6	6	6	6	6	

Note: √= can meet management objective, 0=can't meet management objective

አካባቢው የሚሰጠውን አገልግሎት /Ecosystem services/ **በተሻለ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውል ማስቻል፤ በጎደቤ የተፈጥሮ ደንና አካባቢው የሚነሱ ወንዞችየአካባቢውን ማህበረሰብ በውሃ ምንጭነት የሚያገለግል ሲሆን የአካባቢውን ስርዓተ-ምህዳር ለመጠበቅ ስለሚያስችል የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖዎችን ለመቋቋም ያስችላል።**

ለትምህርትና ሳይንሳዊ ምርምር

በአባሎ-ወይባ /*Combretum-Terminalia* Woodland ስርዓተ ምህዳር ውስጥ የሚገኙ የብዝሃ ህይወት ሃብቶችን በኢትዮጵያና ሱዳን መካከል ሊኖር የሚችል የቱሪስት ፍሰትና የማህበራዊ ግንኙነትን ለማጥናት በአካባቢው ለሚገኘው የጎንደር ዩኒቨርስቲ ህይወታዊ ላቦራቶሪ በመሆን የሚያገለግል ሲሆን አካባቢውን ለስነ ምህዳር ትምህርትና ምርምር ማዕከል በማድረግ በዘርፉ የሚጠበቀውን ሳይንሳዊ ዕድገት ማምጣትና የተፈጥሮ ሃብታችንን አግባብ ባለው መንገድ ማልማትና መጠቀም ያስችላል፣

የተፈጥሮ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መስህቦችን በመጠበቅና በማልማት ለቱሪዝም መጠቀም

የጎደቤ የተፈጥሮ ደን በተፈጥሮአዊና ማራኪ በሆነ የመሬት አቀማመጥ፣በውስጡ ሊጎበኙ የሚችሉ የዱር እንስሳት፣አዕዋፍና እፅዋትን እንዲሁም ንጉስ ዳዊት የጌታን ግማደ መስቀል ከእስክንድሪያ ለማምጣት እንደሄዱ ያረፉበትን የስናርን ተራራ አቅፎ የያዘ በመሆኑ አካባቢውን በመጠበቅና በማልማት ለሰው ልጆች አእምሮ ማደሻ በማድረግ ከነተፈጥሮዊ ገፅታው በማቆየት በውስጡና በአካባቢው ያሉትን ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ሃብቶች በዘለቄታዊ ለቱሪዝም ልማት ጥቅም ላይ በማዋል የተፈጥሮ ሃብቱን ማስጠበቅ የሚቻልበት እድል አለ፡፡

6. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

- **የመስክ ደንብ ልብስና ጫማ አለመኖር**

አካባቢው ቆላማና ደን በመሆኑ ውስጥ ለውስጥ እየተሸሎከሎኩ መስራት የሚጠይቅ ከመሆኑም ባሻገር ነብሳት ጥቃት እንዳያደርሱ የመከላከያ የመስክ ልብሶች የሚያስፈልጉ ቢሆንም የደንብ ልብስ ባለመፈቀዱ አሁንም ለመስክ ስራዎች እንቅፋት በመሆን ላይ ይገኛል፡፡

- **የፀጥታ ችግር**

ለመስክ በተንቀሳቀስንበት ወቅት በተለይም ከጎንደር አብርሃ ጂራ በተጓዝንበት ወቅት መንገድ ከስድስት ስዓት በላይ ተዘግቶብን እስኪከፈት የጠበቅን ሲሆን በግራር ወሃ ቀበሌ በኩል ወደ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ለጥናት በገባንበት ወቅት እኛን ሊያጅቡ የሄዱ ጸረ

ሽምቅ ሚሊሻዎች ከሽፍታ ጋር ተኩስ የገጠሙ ሲሆን በወቅቱ የተወሰነም ቢሆን በስነ-ልቦና ጫና አሳድሮብን ነበር፡፡

7. ወደፊት መከናወን ያለባቸው ስራዎች

በዚህ ጥናት የተዳሰሰው የጎደቤ አካባቢ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ተፈጥሮዊና ስርዓተ ምህዳራዊ ወሳይነቱ ሳይቀየር ጠብቆ ለማቆየትና አግባብ ባለው መልኩ ለማልማትና ለመጠቀም ወደ ጥብቅ ስፍራነት እንዲመጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም በክልሉ መኖር ያለበትን ወሳይ ስርዓተ ምህዳር ሽፋን ከነበረበት 2 ከመቶ ከፍ እንዲልና በ5 ዓመቱ እውን ማድረግ ካለብን 7 ጥብቅ ስፍራዎች አንዱን እንድናሳካ የሚያደርግ ስራ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ይህ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በአዋጅ ህጋዊ ሰውነት የሚያገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ወደ ፊት መከናውን ያለባቸው ተግባራት በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡

የጥናቱን ውጤት ለአጋር አካላት መላክና አስተያየት መቀበል

የዚህን ጥናት ውጤት ለቢሮው በማቅረብ ዝርዝር ውጤቱን በማሳወቅ በቢሮ ደረጃ በማጠቃለያ ሃሳቦቹ ላይ የጋራ መግባባት መፍጠርና የጥናቱን ውጤት ለሚመለከታቸዉ አካላት መላክና አስተያየት መቀበል፣

ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በየትኛው የጥብቅ ስፍራ ደረጃ (protected area category) እንደሚመደብ መወሰን

የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ አካባቢው ለተፈጥሮ ጥብቅ ስፍራነት ያለውን ጠቀሜታ፣ ተስማሚውን የጥብቅ ስፍራ ደረጃ በIUCN የጥብቅ ስፍራዎች ደረጃ (protected area category) መሰረት የትኛውን ምድብ (Protected area category I-VI) መወሰን፡፡ ምንም እንኳን በጥናት ቡድኑ በጥናት እንደተረጋገጠው ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የብዝሃ ህይዎትና ስርዓተ-ምህዳር ጥበቃ ፣የተፈጠሮ፣ባህላዊና ታሪካዊ ሃብቶችን በመጠበቅና በማልማት ለቱሪዝም ልማት የሚያስችል በመሆኑና ከዚህም በተጨማሪ ለትምህርትና ሳይንሳዊ ምርም ግልጋሎት መዋል የሚሉትን የመጀመሪያ ደረጃ አላማዎች የሚያሳካ በመሆኑ Protected area category II (National Park) ሊያሟላ እንደሚችል የተረጋገጠ ቢሆንም የተፈጠሮ ሃብቱን ለማልማትና ለመጠበቅ የተሻለ አጠባበቅ ስርዓት ካለ ከሚመለከታቸው አጋር አካላት አስተያየት መሰብሰብ

የክለላ ስራውን እንደገና ህጋዊ እውቅና መስጠት በሚያስችል መልኩ ማከናወን

በመጀመሪያ ደረጃ የፖቴንሽያል የዳሰሳ ጥናት፣ በሁለተኛ ደረጃ ዝርዝር ጥናት፣ በመጨረሻም

ክለላና ህጋዊ ዕውቅና ማሰጠት አንድን የተፈጥሮ ደን ወደ ጥብቅ ስፍራ ለማምጣት በቅደም

ተከተል የሚከናወኑ የጥናት ስራዎች ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ታሳቢ ጥብቅ ይህን ቅደም ተከተል በመከተል በክልሉ መከናወን እንዳለበት የወረዳው አካላት እየጠየቁ በወረዳ ደረጃ የጥናትና የክለላ ስራ የከናወኑ ቢሆንም የተካሄደው የክለላ ስራ ጉልቶችን ያመላከተ ባለመሆኑና ከተከለለም መኋላ ለኢንቨስትመነት ከተከለለውቦታ ውስጥ የጠመራ በመሆኑ የክለላው ስራ በወረዳ አጋር አካላት እንደገና ሊከናወን ይገባል ይህም ስራ በዚህ አመት ተከናውኖ በአጭር ጊዜ ህጋዊ እወቅና ማሰጠት ካልተቻለ ቦታውን ሳይጠፋ ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

ሕጋዊ እውቅና ማሰጠት

በፖቴንሽያል፣ ዝርዝርና ክለላ ጥናቶች የተገኙትን ማጠቃለያዎች መነሻ በማድረግ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጠቀሜታዎች ለተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ለቱሪዝም ልማት ያላቸውን አስተዋፅዖ በማረጋገጥ የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ዳር ድንበር በህግ እንዲወሰን ከፖቴንሽያል፣ ዝርዝርና ክለላ ጥናቶች የተገኙ የማጠቃለያ ሃሳቦችን የያዘ ደጋፊ ሰነድና ረቂቅ ደንብ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ለውሣኔ ማቅረብና ሕጋዊ ሰውነት ማሰጠት አስፈላጊ ነው ሆኖም ግን የጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ አሁን ከሰሜን ጎንደር ደጋማ አካባቢዎች በተለይም ከጭልጋ፣ላይ አርማጭሆና መተማ ወረዳዎች በሚመጡ ህገወጥ አራሾች ከወረዳውና አጎራባች ወረዳዎች አነዲሁም ከተወሰኑ የትግራይ ክልል ወረዳዎች በሚመጡ የቤት እንስሳት ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት በመሆኑ በአስቸኳይ ህጋዊ እውቅና አግኝቶ የጥበቃ ስርዓቱ ካልተጠናከረ ሃብቱን ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል፣

የመሠረተ ልማትና የግንባታ ቦታዎችን መለየትና ግብዓት ማፈላለግ

ለጥበቃና ልማት በሚያመቸው የጥብቅ ስፍራዎች ደረጃ (IUCN criteria for protected area category II) ታሳቢ የብሄራዊ ፓርኩ በጥብቅ ስፍራነት የሚከለልና ህጋዊ ሰውነት የሚሰጠው ከሆነ ከጽ/ቤት ግንባታ ጀምሮ ለጥበቃና ለተፈጥሮ ሃብት ልማት አስፈላጊ የሆኑ የመሠረተ ልማትና የግንባታ ቦታዎችን በጥናት መለየትና አስፈላጊውን ግብዓት ለማሟላት የገንዘብ ድጋፍ ማፈላለግና የግንባታ ስራዎችን በማከናወን የልማትና ጥበቃ ስራወን ማሳለጥ ያስፈልጋል፡፡

የአጋር አካላትን ተሳትፎ፣ ተግባራትና ኃላፊነቶች መለየትና ማሳወቅ

በተለያዩ የጥናት፣ የጥበቃና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች የሚመለከታቸውን አጋር አካላት ማሣተፍ፣ ማሳወቅና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡና ዘላቂ አጋርነታቸውን ለማረጋገጥ፣ ወቅታዊ ግንኙነትና ተግባራዊ እንቅስቀሴ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ይህንም ማረጋገጥና ለጋራ ውጤት በጋራ መስራት ያስፈልጋል፣

8. የጉዳዩ ባለቤቶችና የባለድርሻ አካላት ተግባራትና ኃላፊነት ትንተና

ከላይ በዝርዝር የተቀመጡና ወደፊት መከናወን ያለባቸው ሌሎች አስፈላጊ ስራዎችን ለማሳካት የጉዳዩ ባለቤቶችና ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት በተፈለገው መጠንና ጊዜ መወጣት ይኖረባቸዋል፡፡ ስለዚህ ከላይ በዝርዝር ለተቀመጡና ወደ ፊት መስራት ላለባቸው ስራዎች ወሳኝና አጋር ናቸው ተብለው የተመረጡ ባለድርሻ አካላትና የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤቶች ተግባርና ኃለፊነት ተለይተው እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

የባህልና ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ

በአዋጅ በተሠጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት በቢሮው ለስራው ቀጥተኛና ተጠሪነት ያለዉ የዱር እንሰሳት ጥናት፣ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የስራ ሂደት በዋናነት የሚከተሉትን ተግባራት ይፈጽማል

- የተፈጥሮ ሃብቱ ጉዳት እንዳይደርስበት የህጋዊ ሰውነት እስኪያገኝ ድረስ ቦታው የክትትልና ጥበቃ ስራ እንዲከናወንለት የሚመለከታቸውን አጋር አካላት ያስገነዝባል፤
- ቦታው በርሃማነትን ለመከላከልና የብዝሃ ህይወት ሃብትን ለመጠበቅ የሚያስችል በመሆኑ የጥብቅ ስፍራ ደረጃ አግኝቶ እንዲጠበቅ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል
- በቦታው ላይ ተጨማሪ ጥናቶች እንዲካሄዱ የማስተባበር ሚና ይኖረዋል ጥናት ያካሂዳል
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የጎደቤ የተፈጥሮ ደን ለወደፊት ስለሚደረግለት የጥበቃ ስርዓት ረቂቅ ደንብና ደጋፊ ሰነዶችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አጋር አካላት በማቅረብ አስተያየት ያሰባስባል
- የተፈጥሮ ደኑ በአዋጅ ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ አስፈላጊ ስራዎችን ያከናውናል
- የሚያስፈልግ የሰው ኃይልን ሰርቶ ለሲቪል ሰርቪስ ቢሮ በማቅረብ መዋቅር ማስፈቀድ

- ህጋዊ ሰውነት ካገኘ በኋላ የጥበቃ ስርዓቱን የሚያስተባብር ጽ/ቤት እንዲቋቋም ይሰራል፡፡

የሰሜን ጎንደር ዞን ግብርና መምሪያ

- በአካባቢው ላይ ልቅ ግጦሽ ከፍተኛ ጫና እያደረሰ በመሆኑ ከተለያዩ አካባቢዎች ወደ ቦታው ለግጦሽ የሚደረግ እንቅስቃሴ የሚቀንስበትን ብሎም የሚቆምበትን ስርዓት መዘርጋት
- በቆላማው አካባቢ እየተካሄደ ያለው እሳት በመለኮስ አካባቢው እየተጎዳ በመሆኑ የሚቆምበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- ከክልል በሚመደብ በጀት አካባቢውን አሁንም እያስጠበቀ በመሆኑ ህጋዊ እውቅና አግኝቶ የጥበቃ ስርዓቱ እስኪጠናከር ድረስ የጥበቃ ስራው እንዲቀጥል ማስቻል
- ለመጥፋት በተቃረቡ ለምሳሌ እንደ ዞቢ በመሳሰሉ የዱር እጽዋት ላይ ህገወጥ በሆነ መልኩ ወደ ሱዳን የሚደረግ ንግድ እንዲቆም መስራት
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲጎለብት የበኩልን አስተዋጾ ማበርከት
- በአካባቢው ባሉ የባለሃብት እርሻዎች ላይ አደገኛ አረሞች እየተስፋፉ ስለሆነ በአካባቢው ላይ የበለጠ ጉዳት ሳያደርሱ ክትትል ማድረግ

የሰሜን ጎንደር ዞን አካባቢ ጥበቃ፣መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር መምሪያ

- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ዙሪያ ለኢነቨስትመንት እርሻ የተሰጣቸው ባለሃብቶች የእርሻ መሬታቸውን ህገ-ወጥ በሆነ መልኩ ወደ ተፈጥሮ አካባቢው እያስፋፉና ጫና እየፈጠሩ በመሆናቸው እርሻን ከማስፋፋት ይልቅ ምርታማነትን ሊጨምር የሚችሉ ተግባራትን እንዲያከናወኑ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- በአካባቢው ያለው ህገወጥ የእርሻ መስፋፋትንና ከደጋማና አጎራባች ወረዳዎች ወደ አካባቢው የሚደረግ ህገወጥ እርሻ የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት እየጎዳ በመሆኑ የሚቆምበትን ስትራቴጅ መዘርጋት
- አካባቢው በልቅ ግጦሽ፣በሰደድ እሳት፣በህገ-ወጥ እርሻ ምግንያቶች ተጽዕኖዎችን እያስተናገደ በመሆኑ በአካባቢው የተጽዕኖ ግምገማ በማካሄድ ተስማሚ መፍትሄዎችን መስጠት
- በአካባቢው ባሉ የባለሃብት እርሻዎች ላይ አደገኛ አረሞች እየተስፋፉ ስለሆነ በአካባቢው ላይ የበለጠ ጉዳት ሳያደርሱ ክትትል ማድረግ
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲጎለብት የበኩልን አስተዋፅዖ ማበርከት

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ

- አካባቢው ህይወታዊ ላብራቶሪ ሆኖ ሊያገለግል ስለሚችል የአካቢውን የተፈጥሮ ሃብት፣ በአካባቢው ላይ ያሉ ተጽዕኖዎችን፣የአካባቢውን ህብረተሰብ አኗኗር፣በተፈጥሮ ኃብቱና በአካባቢው ህብረተሰብ የሚከሰቱ ግጭቶችንና የመሳሰሉ ጥናቶችን ያደርጋል፣
- ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፋቸውን ሲያዘጋጁ በአካባቢው ላይ እንዲሰሩ ያደርጋል
- ሌሎች አስፈላጊ የምርምር ስራዎችን ያከናውናል
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲጎለብት የበኩሉን አስተዋጸ ማበርከት

የሰሜን ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ

- የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ህጋዊ እውቅና ማግኘት እንዲችል የዞንና የወረዳ ተቋማትን ያስተባብራል
- በአካባቢ ያሉ የመስብ ሃብቶች እንዲለሙና መረጃቸው በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል
- የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ህጋዊ እውቅና ለማሰጠት የሚደረጉ አውደጥናቶችን ያሰተባብራል
- የታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን ለማቋቋም በሚደረጉ ጥረቶች ዋነኛ ተዋናይ በመሆን ይሰራል
- በወረዳው ዋነኛው የመስህብ ሃብት በመሆኑ ኢኮ-ቱሪዝም እንዲስፋፋና የአካባቢው ህብረተሰብ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሰራል
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጂታዊ አሰራር እንዲጎለብት የበኩልን አስተዋፅየ ማበርከት

የሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደርና ጸጥታ ጉዳዮች ጽ/ቤት

- በተፈጥሮ አካባቢው የሚከሰቱ ህገወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል ይቻል ዘንድ ለወረዳ አስተዳደርና ጸጥታ ጉዳዮች ጽ/ቤት መመሪያዎችንና የአሰራር አቅጣጫዎችን ያስተላልፋል
- ወደ አካባቢው የቤት እንስሳትን ከተለያዩ ወረዳዎች ይዞ መንቀሳቀስና የህገወጥ እርሻ መስፋፋት በአካባቢው የተፈጥሮ ሃብት ከመጉዳቱ በተጨማሪ የመልካም አስተዳደር ችግር እየሆነ በመምጣቱ ችግሩ እንዲፈታ የበኩሉን ይሰራል፡፡

በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አጎራባች ወረዳዎች አስተዳደር ጽ/ቤቶች

- የጎደቤ ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክን በተመለከተ ለአካባቢው ማኅበረሰብ የግንዛቤ መድረኮችን በማዘጋጀት የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር
- የጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ክለላ እንዲጠናቀቅ የማስተባበር ሚናውን ይወጣል

- ህገወጥ እርሻ እንዳይሰፋፋና ወደ አካባቢው የሚደረግ ህገወጥ የቤት እንስሳት ፍሰት እንዲቆም የማስተባበር ሚናውን ይወጣል
- አካባቢውን በዘላቂነት ለማልማትና ለመጠቀም አካባቢውን የብሄራዊ ፓርክነት ደረጃ ሰጥቶ መከለል፣ ማልማትና መጠበቅ ይገባል፡፡ በመሆኑም በያሉበት ወረዳ የሚካሄደውን ተግባራትን ይመራሉ ያስተባብራል
- በወረዳው ውስጥ ያሉ አጋር አካላት ለታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ጥበቃ የበኩላቸውን እንዲያበረከረቱ ይመራል ያስተባብራል
- በአካባቢው ለመጥፋት የተቃረቡ እጽዋትና የዱር እንስሳት እንዳይነገዱ የበኩሉን ይሰራል፡፡
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጂታዊ አሰራር እንዲጎለብት ተቋማትን ያስተባብራል

በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አጎራባች ወረዳዎች ግብርና ጽ/ቤቶች

- አካባቢው አሁን እየደረሰበት ባለው የጭፍጨፋ ጫና የአካባቢው ልዩ መገለጫ መሆኑን እያጣ መጥቷል በመሆኑም ህገወጥ የደን ጭፍጨፋ እንዲቀንስ ብሎም እንዲጠፋ ይሰራል፡፡
- በአካባቢው ላይ ልቅ ግጦሽ ከፍተኛ ጫና እያደረሰ በመሆኑ በአካባቢው ላይ የልቅ ግጦሽ ስርዓት የሚቀንስበትን ብሎም የሚቆምበትን ስራ ተግባራዊ ያደርጋል
- በቆላማ አካባቢዎች እየተካሄደ ያለው የእጣንና ሙጫ ምርት የአካባቢው ስርዓተ ምህዳር እንዳይጎዳ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተገቢውን ስልጠና መስጠትና ተገቢውን ክትትል ማድረግ
- ከክልል በሚመደብ በጀት አካባቢውን አሁንም እያስጠበቀ በመሆኑ ህጋዊ እውቅና አግኝቶ የጥበቃ ስርዓቱ እስኪጠናከር ድረስ የጥበቃ ስራው እንዲቀጥል ማስቻል
- በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አዋሳኝ መሬት ያላቸው ባለሃብቶች ማሳቸውን እንዲንከባከቡና ምርታማነታቸውን እንዲጨምሩ መስራት፣
- በአካባቢው እየተከሰተ ያለው የደን ቃጠሎ ለአካባቢው የተፈጥሮ ሃብት ውድመት በዋነኛነት የሚጠቀስ በመሆኑ እንዲቆም የበኩልን መስራት
- በአካባቢው የሚካሄድ ማንኛውንም የህገ ወጥ አደን እንቅስቃሴ እንዲቆም ማድረግ
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጂታዊ አሰራር እንዲጎለብት የበኩልን አስተዋጸ ማበርከት

በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አጎራባች ወረዳዎች አካባቢ ጥበቃ፣መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ጽ/ቤቶች

- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ዙሪያ ለኢንቨስትመንት እርሻ የተሰጣቸው ባለሃብቶች የእርሻ መሬታቸውን ህገ-ወጥ በሆነ መልኩ ወደ ተፈጥሮ አካባቢው እያስፋፉና ጫና እየፈጠሩ በመሆናቸው እርሻን ከማስፋፋት ይልቅ ምርታማነትን ሊጨምር የሚችሉ ተግባራትን እንዲያከናወኑ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- የጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ክለላ እንዲጠናቀቅ የሚጠበቅበትን ይሰራል
- በቆላማ አካባቢዎች እየተካሄደ ያለው የእጣንና ሙጫ ምርት የአካባቢው ስርዓተ ምህዳር እንዳይጎዳ የኢንቨስትመንት ፍቃድ የተሰጣቸው ባለሃብቶች ሃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ማስገንዘብና አመራረቱ በአካባቢው ላይ ያለውን ተፅዕኖ መከታተል
- በአካባቢው ያለው ህገወጥ የእርሻ መስፋፋትንና ከደጋማ አካባቢዎች ወደ ቆላማ አካባቢዎች የሚደረግ ፍልሰት የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት እየጎዳ በመሆኑ እንዲቆም ስራዎችን መስራት
- አካባቢው እንደመቀነት በመሆን የሳህሊያንን በርሃ ለመከላከል ሲያገለግል የቆየ ቢሆንም አሁን መቀነቱ በመቆረጡ የበለጠ ጉዳት እንዳይደርስ አካባቢው የሚጠበቅበት የበርሃነት መስፋፋት እንዲቆጣጠር የደን ጭፍጨፋ እንዲቆም የበኩልን መስራት
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጂታዊ አሰራር እንዲጎለብት የበኩልን አስተዋፅዖ ማበርከት

በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አጎራባች ወረዳዎች ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች

- የጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክና አካባቢ ወደጥብቅ ስፍራነት ለማምጣት በሚደረጉ ስራዎችን ከወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ጋር በመሆን በአስተባባሪነት ይመራል
- የጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ክለላ እንዲጠናቀቅ የሚጠበቅበትን ይሰራል
- በአካባው እየተከናወነ ያለው ልቅ ግጦሽ፣ህገወጥ እርሻና ሰደድ እሳት እንዲቆም የበኩሉን ይሰራል
- በአካባቢ ያሉ የመስብ ሃብቶች እንዲለሙና መረጃቸው በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል
- የአካባቢው ህብረተሰብ ከኢኮ ቱሪዝም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሰራል
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጂታዊ አሰራር እንዲጎለብት የበኩልን አስተዋፅዖ ማበርከት

በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አጎራባች ወረዳዎች ሚሊሽያ፣ ፖሊስ ጽ/ቤቶች እና ሌሎች የጸጥታ አካላት

- በተፈጥሮ አካባቢው የሚከሰቱ ህገወጥ ድርጊቶችን እንደ ህገወጥ እርሻ መስፋፋት፣ ልቅ ግጦሽ፣ ህገ ወጥ አደንና የደን ጭፍጨፋ እንዳይስፋፋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር

በመሆን የመከላከል ስራውን እየሰራ ያለው የጸጥታ አካሉ በመሆኑም አሁንም አስፈላጊውን መርሃግብር በማዘጋጀት የመከላከል ስራ ይሰራል

- በተፈጥሮ አካባቢው የሚከሰቱ ችግሮችን ለመከላከል በጉዳዩ ላይ የፍትህ አካላት ጉልህ አስተዋጸ እንዲያበረክቱ ወንጀሎችን በማጣራትና በመከላከል የበኩሉን ይሰራል
- በአካባቢው ህገወጥ የሆነ የዱር እስሳትና ዱር እፅዋት ወጤቶች ንግድ እንዳይስፋፋ የበኩሉን ይሰራል
- በአጠቃላይ በአካባቢው ላይ የሚከሰቱ ህገወጥ ድርጊቶችን የመከላከል ስራው ላይ ያለው ሚና የማይተካ በመሆኑ አሁንም አጠናክሮ ሊሄድበት ይገባል

በአካባቢው ነዋሪዎች መከናወን ያለባቸው

የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ከ6 ቀበሌዎች ጋር የሚዋሰን ሲሆን የእነዚህ ቀበሌዎች የአካባቢ ነዋሪዎች በአካባቢው እየተካሄደ ያለውን ልቅ ግጦሽ፣ የደን ምንጠራና የደን ቃጠሎ ለማስቀረት ከፍተኛ አስተዋጸ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ህብረተሰቡ የተፈጥሮ ደኑና የዱር እንስሳቱ ባለቤት በመሆኑ ለትዉልድ የማስተላላፍ ግዴታም ስላለበት የአጎራባች ቀበሌ ነዋሪዎችና የቀበሌ አመራር አባለት ሃብቱ ወደትውልድ እንዲተላለፍ የበኩላቸውን መስራት ይጠበቅባቸውል፡፡

ፀ.ዋቢ መጽሐፍት (References)

1. Abeje Eshete, Demel Teketay and Hulten, Hakan, H. (2005). The Socio-Economic Importance and Status of Populations of *Boswellia papyrifera* (Del.) Hochst in Northern Ethiopia: The Case of North Gondar Zone. *Forests Trees and Livelihoods*, 15: 55-74,
2. Abraham Marye, Mekete Desie ,Shimels Aynalem , Endalkachew Teshome, Getachew Tamiru , Getachew Tesfaye (2009), Alatish National Park General Management Plan,ANRS Parks Development and Protection Authority, Bahir Dar ,Ethiopia
3. Abraham Marye, Berhanu Gebre, Daregot Berihun ,Desalegn Ejigu,Dereje Tewabe, Tesfaye Mekonen (2008), Wildlife and Socioeconomic Status of Alatish National Park (ALNP), ANRS Parks Development and Protection Authority, Bahir Dar , Ethiopia
4. Abrham Marye, (2011).Major Natural Attractions of the Amhara Region. Culture And Tourism Bureau, Bahir Dar, Ethiopia
5. ANRS CTP'sD Bureau (2009), Guide to natural attractions of Simien Mountains and Alatish National Park's of North Gondar.
6. Azene Bekele Tesema (1993). Useful Trees and Shrubs for Ethiopia: Identification, Propagation and World Agroforestry Center, RELMA, ICRAF Eastern Africa Region, Nairobi, Kenya.
7. Azene Bekele Tesema (2007). Useful Trees and Shrubs for Ethiopia: Identification, Propagation and Management for 17 agroclimatic zones. World Agroforestry Center, RELMA, ICRAF Eastern Africa Region, Nairobi, Kenya.
8. Chane Gebeyehu (2000). Land Use and Spatial Distribution of Two Gum and Incense producing Tree Species. A Thesis Submitted in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Science in Range Management in the Faculty of Agriculture University of Nairobi. Wogidi, Ethiopia.
9. Clements, J.F, (2007). The Clements checklist of birds of the world, 6th edition, Cornell University press
10. Daan Vreugdenhil, Ian J. Payton, Astrid Vreugdenhil, Tamirat Tilahun, Sisay Nune, Emily Weeks (2012), Carbon Baseline and Mechanisms for Payments for Carbon Environmental Services from Protected Areas in Ethiopia, Addis Ababa, Ethiopia

11. Dharani N. (2005), Filed guide to common trees and shrubs of east Africa, Hirt& Carter cape (pty) ltd., Cape Town
12. Ervin, J., N. Sekhran, A. Dinu, S. Gidda, M.Vergeichik and J. Mee, (2010), Protected Areas for The 21st Century: Lessons from Undp/Gef's Portfolio. United Nations Development Programme and Montreal: Convention on Biological Diversity.
13. EWNHS (1996). Important Bird Areas of Ethiopia: a first inventory. Ethiopian Wildlife and Natural History Society. Addis Ababa, Ethiopia.
14. FAO of UN (1984). Vegetation and Natural region and their significance for land use planning: report paper for the government of Ethiopia, United Nations development program, technical report 4. AG: DP/ETH178/0031 Rome Italy
15. IBC (2005), National Biodiversity strategy of Ethiopia, IBD, Addis Ababa, Ethiopia
16. IUCN (1994). The IUCN Guideline for protected area management categories.
17. IUCN (1996). Managing protected area in the tropics.
18. John G.Williams and N. Arlott, (1980). A field Guide to the birds of East Africa,

    Collins St James place, London.

19. Kahsay Berhe (2004) land use and land cover changes in the central highlands of Ethiopia: the case of Yerer Mountain and its surrounding a thesis submitted to the school of graduate studies, Addis Ababa University.
20. Kumera Wkjira and Zelalem Tefera (eds) (2005). Wildlife Management. Parks Development and protection Authority: Compendium of notes on wildlife conservation and Management A training manual for park management and project experts, Bahir dar, Ethiopia
21. Naughton-Treves, L., M., B. Holland and K.Brandon, (2005), The Role of Protected Areas In Conserving Biodiversity And Sustaining Local Livelihoods. Down Loaded From Arjournal, Annual Reviews Org. By University Of California
22. Redman.N,Stevenson.T and Fanshawe (2009) Birds of Horn Africa,C&C offset printing COLtd,Chaina
23. Safari Patrol: Species list: Trees and shrubs of East Africa at http://www.safaripatrol.com/species_trees.shtml
24. Tesfaye Awas (unpublished),Endemic plants of Ethiopia: Preliminary working list to contribute to National plant conservation target, Addis Ababa
25. Tesfaye Awas (2007), Plant Diversity in Western Ethiopia: Ecology, Ethnobotany and Conservation; Dissertation presented for the degree of Doctor of Philosophy,

Department of Biology Faculty of Mathematics and Natural Sciences ,University of Oslo, Norway

26. UNEP (1992), Conventions on biological diversity, No.30619, Rio de Janeiro
27. Walter,K.S.and Gillett, H.J. (1998), 1997 lUCN Red List of Threatened Plants, lUCN, Gland, Switzerland and Cambridge, UK
28. Wolde Michael Kelecha (1987), *A Glossary of Ethiopian plant names*, 4th edition, Addis Ababa, Ethiopia
29. ??? (2011) ,Ethiopia's Climate-Resilient Green Economy Green economy strategy , Addis Ababa, Ethiopia
30. **ሰለሞን ይርጋ (2000) አጥቢዎች አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**
31. **የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም አጭር ታሪክ** (2005 **ዓ.ም**) **በማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የተዘጋጀ**
32. **የሰሜን ጎንደር አሰ. ዞን የቱሪስት መስሕብ ሃብቶች በከፊል** (**መስከረም** 2002 **ዓ.ም**) **በሰሜን ጎንደር ዞን ባ/ቱ/መምሪያ የተዘጋጀ**
33. **ሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ** 21**ኛ ዓመት ቁጥር** 7 **የካቲት** 2006 **ዓም ማኅበረ ቅዱሳን**
34. **ስንክሳር የዲያቆን መልአኩ እዘዘው ድረ ገጽ** (Monday, July 25, 2011) **አርባ አራቱ ታቦታተ ጎንደር**
35. **የዳንኤል ክብረት ዕይታዎች ድረ ገጽ** (Wednesday, December 19, 2012) **ከጣራ እስከ ጉዛራ**
36. **ወ/ሮ ዘውዴ ገ/እግዚአብሔር**(2006 **ዓ.ም**) **ቅዱስ መስቀል በኢትዮጵያ አርቶዶክስ አስተምህሮ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**
37. **ተክለጻድቅ መኩሪያ**(1958 **ዓ፣ም**) **የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል፣ አዲስ አበባ**
38. **ዲ/ን ዮሐንስ ሰለሞን** (2001 **ዓ.ም**) **የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት፣ አዲስ አበባ**
39. **የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ጥናት**(2006 **ዓ.ም**) **በባ/ቱ/ፓ/ል/ቢሮ የተዘጋጀ**

እዝል1. በጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በጥናት ወቅት የተለዩ ዕፅዋት

No.	Botanic name	Local name
1.	*Abelmoschus ficuleneus*	wayika
2.	*Acacia polyacantha*	Gumero
3.	*Acacia senegal*	Mogn Gumero
4.	*Acacia seyal*	Key girar
5.	*Adansonia digitata*	Diza
6.	*Agava spp.*	Beska
7.	*Albizia malacophylla*	Mera
8.	*Albizia amara*	Dulesa
9.	*Anogeissus leiocarpa*	Kirkira
10.	*Asparagus africanus*	Yeset kesit
11.	*Azadirachta indica*	Neem
12.	*Balanites aegyptiaca*	Mekie
13.	*Boswellia papyrifera*	Walia meker
14.	*Breonadia salicina*	Dembeka
15.	*Calotropis procera*	Tobia
16.	*Cissus populnea*	Nechi liza hareg
17.	*Cissus qudrangularis*	Alkie Hareg
18.	*Clematis longicauda*	azo hareg
19.	*Combretum aculeatum*	Forha/sebeha
20.	*Combretum adenogonium*	Kongera
21.	*Combretum collinum*	Chamda

No.	Botanic name	Local name
22.	*Combretum molle*	Abalo
23.	*Corchorus olitorius*	Melekuya
24.	*Dalbergia melanoxylon*	Zobi
25.	*Dichrostachys cinerea*	Gorgoro
26.	*Diospyros mespiliformis*	Serkin
27.	*Dombeya spp*	Neftelo
28.	*Erythrina abyssinica*	Kuara
29.	*Fics palmata*	Chibeha
30.	*Ficus sur*	Shoal
31.	*Ficus sycomorus*	Bamba
32.	*Flueggea virosa*	Arena
33.	*Gardenia ternifolia*	Gambilo
34.	*Grewia bicolar*	Sumaya
35.	*Grewia ferruginea*	Lnquata
36.	*Grewia mollis*	Lnquata
37.	*Hyphaene thebaica*	Zenbaba /laha
38.	*Jatropha curcas*	Jatropha
39.	*Kigelia africana*	Adendin
40.	*Lanchocarpus laxifiora*	Hamija /Zengerifa
41.	*Lannea fruticosa*	Fola
42.	*Lannea welwitschii*	Dergeja
43.	*Maytenus undata*	Kukba /Atat
44.	*Ocimum lamiifolium*	Damakesie

No.	Botanic name	Local name
45.	*Oxytenanthera abyssinica*	shimel
46.	*Piliostigma reticulatum*	Alasha
47.	*Piliostigma thonningii*	Dawda
48.	*Pittosporum viridifolium*	gala zabia
49.	*Pterocarpus lucens*	Chara
50.	*Salix spp*	wonz adimik
51.	*Securidaca longepedunculata*	shutera /etsemenahi
52.	*Securinega virosa*	Shasha
53.	*Solanum incanum*	Embuay
54.	*Steganotaenia araliacea*	yejib dula
55.	*Sterculia africana*	Darle
56.	*Stereospermum kunthianum*	Zana
57.	*Tamarindus indica*	Kumr
58.	*Terminalia brownii*	Woyiba
59.	*Terminalia laxiflora*	Wonbela
60.	*Vernonias pp*	Girawa
61.	*Ximenia americana*	Enkoy
62.	*Ziziphus mauritiana*	Abeterie
63.	*Zizipus spina-christ*	Gaba
64.	*Hyparrhenia subplumosa*	Jingra
65.	*Striga hermonthica*	Akencira /Metelem
66.	*Sorghum arundiaceum*	sudan grass/Jora
67.	*Hyparrhenia cynescence*	topaz grass

No.	Botanic name	Local name
68.	*Hygrophila auriculata*	Amekila
69.	*Sorghum versicolor*	Sembelet
70.		Ashama
71.		Workina
72.		Enkudkuda
73.		Betremusie
74.		Yewosfat enchet
75.		Yetota Enkudkuda
76.		Yeahiya abish
77.		gershema /yeferes zenig mesay
78.		mizane/ Kine mebrat
79.		Yebre Gomen
80.		yeahya abish
81.		Merta /yekaila enchet

እዝል2. በጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በጥናት ወቅት የተለዩ የዱር እንስሳት

No.	Scientific Name	Common Name	Conservation status
1.	*Canis aureus*	Golden (common) Jackal	Lc
2.	*Caracal caracal*	Caracal	LR/lc
3.	*Ceropithecus aethiops*	Vervet Monkey	LR/lc
4.	*Civettics civetta*	African civet cat	LR/lc
5.	*Crocuta crocuta*	Spotted hyena	LR/lc

No.	Scientific Name	Common Name	Conservation status
6.	*Erythrocebus patas*	Patas monkey	LR/lc
7.	*Felis lybica*	African wild cat	LR/lc
8.	*Felis serval*	Serval cat	LR/lc
9.	*Funisciurus spp.*	squirrel	
10.	*Hystrix cristata*	Porcupine	LR/lc
11.	*Lepus capensis*	Cape hare	
12.	*Mellivora capensis*	Ratel (Honey badger)	VU
13.	*Orycteropus afer*	Aardvark	EN
14.	*Ourebia ourebi*	Oribi	LR/cd
15.	*Panthera pardus*	Leopard	LR/lc
16.	*Papio anubis*	Anubis baboon	LR/cd
17.	*Phacochoerus africanus*	warthog	LR/lc
18.	*Procavia capensis*	Rock hyrax	LR/lc
19.	*Sylvicapra grimmia*	common duiker	LR/lc
20.	*Tragelaphus scriptus*	Common bushbuck	LR/lc
21.	*Tragelaphus strepsiceros*	Greater kudu	LR/cd
22.	*Python sebae*	African rock python	
23.	*Varanus salvadorii*	Monitor lizard	Appendex II
24.	*Naja haje*	Egyptian cobra	
25.		Different lizards	
26.		Different fish species	

እዝል3. በጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በጥናት ወቅት የተለዩ አዕዋፍት

No.	Common Name	Scientific Name	Status
1.	Egyptian Goose	*Alopochen aegyptiacus*	
2.	Grey heron	*Ardea cinera*	
3.	Hadada ibis	*Bostrychia hagedash*	
4.	Abyssinian ground hornbill	*Bucorvus obyssinicus*	
5.	Grasshopper Buzzard	*Butastur rufipennis*	
6.	Nubian woodpecker	*Campethera nubica*	
7.	Senegal Coucal	*Centropus superciliosus*	
8.	pied Kingfisher	*Ceryle rudis*	
9.	Speckled Pigeon	*Columba oliviae*	
10.	Abyssinian roller	*Coracias abyssinica*	
11.	Scally francolin	*Francolinus squamatus*	
12.	Lesser Honey Guide	*Indicator minor*	
13.	Lizard buzzard	*Kaupifalco monogrammicus*	
14.	African fir finch	*Lagonostica rubricata*	
15.	Greater blue eared starling	*Lamprotornins chalybeus*	
16.	Dark Chanting Goshawk	*Melierax metabates*	
17.	Eastern Chanting Goshawk	*Melierax poliopterus*	
18.	Black Kite	*Milvus migrans*	
19.	White wagtail	*Motacilla clara*	
20.	Helmeted Guineafowl	*Numida meleagris*	
21.	Namaqua Dove	*Oena capensis*	

No.	Common Name	Scientific Name	Status
22.	Green wood- hoopoe	*Phoeniculus prupures*	
23.	Meyer's Parrot	*Poicephalus meyeri*	
24.	Rose ringed parakeet	*Psittacula krameri*	
25.	Common Bulbul	*Pycononotus barbatus*	
26.	Hamarkob	*Scopus umbretta*	
27.	African mourning Dove	*Streptopelia decipiens*	
28.	African collared Dove	*Streptopelia roseogrisea*	
29.	African grey horn bill	*Tockus nasustus*	
30.	Bruce green pigeon	*Treron waalia*	
31.	African Hoopoe	*Upupa(epops) african*	
32.	Malachite Kingfisher	*Alcedo cristata*	
33.	Verreaux's Eagle-Owl	*Bubo lacteus*	
34.	Cattle Egret	*Bubulcus ibis*	
35.	Red-billed Oxpecker	*Buphagus erythror thnchus*	
36.	Lilac-breasted Roller	*Coracia caudatus*	
37.	Rufous-croened Roller	*Coracias naevius*	
38.	White-bellied go-away bird	*Corythaixoides leucogaster*	
39.	Eastern Grey Plantain eater	*Crinifer zonurus*	
40.	Fork-tailed Drongo	*Dicrurus adsimilis*	
41.	Red-footed Falcon	*Falco vespertinus*	*NT*
42.	White -backed vulture	*Gyps africanus*	*EN*
43.	Long-crested Eagle	*Lophaetus occipitalis*	
44.	Northern Carmine Bee-eater	*Merops nubicus*	

No.	Common Name	Scientific Name	Status
45.	Yellow-billed kite	*Milvus (migrants) aegyptius*	
46.	Swainson's Sparrow	*passer swainsonii*	
47.	White -crested Helmet Shrike	*Prionops plumatus*	
48.	Four-banded Sandgrouse	*Pterocles quadricinctus*	
49.	Laughing Dove	*Strepetopelia rsenegalensis*	
50.	Dusky Turtle Dove	*Streptopelina*	
51.	White-cheeked Turaco	*Tauraco leucotis*	
52.	African Paradise-Flycatcher	*Terpsiphone viridis*	
53.	Sacred Ibis	*Threskiornis aethiopicus*	
54.	Red-billed Hornbill	*Tockus erythrorhynchus*	
55.	White-headed Babbler	*Turdoides leucocephala*	
56.	Red-cheeked Cordon blue	*Uraeginthus bengalus*	
57.	Spur-winged Plover	*Vanellus spinosus*	

ዕዝል 5 በጎደቤ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክና አካባቢው ጠቃሚ የሆኑ ዋና ዋና የጂፒኤስ ነጥቦች/ንባቦች

waypoint	X	Y	Z(M)	remark
1	227296	1490219	652	አብርሃ ጅራ ከተማ
2	209032	1474372	851	የአባይ የክብት ካምፕ ወንዙ ላይ
3	209750	1473030	839	የአቶ አማረ የክብት ካምፕ
4	209859	1473011	848	የእርሻ ማሳ
5	210363	1472559	859	
6	210531	1472510	480	የእርሻ ማሳ
7	210822	1472352	834	
8	210578	1472279	842	የእርሻ ማሳ
9	210222	1472166	830	ሽመል ዛፍ የተገኘበት

				ቦታ/ወንዙ አጠገብ
10	209928	1472428	831	
11	209903	1471951	826	
12	209925	1471726	825	ግራር በብዛት የለበት
13	209353	1470931	826	ወፍ የለበት ቦታ
14	209463	1470660	822	የጥጥ ማሳ
15	209551	1470383	817	የእረሻ ማሳ
16	209884	1470187	806	የእረሻ ማሳ
17	210259	1469835	799	
18	210341	1469774	794	ጎደቤ ወንዝ
19	210736	1470129	787	
20	210824	1470135	789	የእርሻ ማሳ በ2005
21	211241	1470498	784	የእርሻ ማሳ
22	210441	1471496	807	
23	210113	1472091	824	
24	209562	1472323	847	የከብት በረት
25	209160	1471694	831	
26	208758	1471028	880	ተራራዋ አናት
27	208289	1470703	877	
28	207833	1470482	851	
29	207514	1470062	892	ወፍ የለበት ቦታ
30	207314	1469623	988	
31	207336	1469482	1001	ተራራዋ አናት
32	206886	1469597	998	
33	206503	1469746	1002	
34	206283	1470057	1000	
35	206248	1470309	986	
36	206516	1471037	941	
37	207035	1471140	943	
38	207249	1471453	898	
39	208382	1471966	855	
40	209984	1490568	653	ኮርሁመር ቀበሌ
41	205019	1478370	815	የአባ ለጋስ የከብት ካምፕ
42	205513	1477742	841	የእርሻ ማሳ
43	206058	1477816	919	
44	206150	1477567	964	
45	206478	1477201	971	
46	206544	1477095	972	የእርሻ ማሳ
47	206735	1476799	1036	
48	206692	1476737	1040	
49	206542	1476577	1021	
50	206506	1476478	983	የእርሻ ማሳ

51	206794	1475908	935	
52	207091	1475375	935	
53	206705	1475638	946	
54	206362	1475828	952	
55	206139	1475888	955	
56	205444	1476287	983	
57	205362	1477309	855	
58	203022	1478116	782	
59	213815	1472347	779	መንደር
60	213366	1472231	828	
61	212847	1472364	818	የእርሻ ማሳ
62	212619	1472349	787	
63	211996	1471667	792	
64	211785	1471327	821	
65	211610	1470681	786	የእርሻ ማሳ
66	211808	1470140	811	
67	211778	1469810	810	የከብት በረት ቦታ
68	212645	1469606	810	
69	213090	1469716	843	
70	212698	1470649	786	
71	213390	1471268	769	
72	214127	1472034	754	
73	214177	1472389	762	የአቶ ሃይሌ ካፕ
74	213594	1472785	776	
75	213152	1473221	782	
76	212953	1473374	788	
77	212584	1473334	834	
78	212067	1473745	892	ተራራዋ አናት
79	222526	1476354	713	ድርማገ ቀበሌ
80	219265	1485648	705	ግራር ውሃ ቀበሌ
84	202292	1449422	869	ቁጥር 1
85	205247	1440544	738	ሽመላ ጋራ
86	201956	1429538	705	ጓንግ ወንዝ ድልድይ
87	198133	1427334	735	አስፓልቱ መገንጠያ